# *ምዕራፍ አሥራ ሁለት*

# ጄኒ



ብዙ ኪሎ ሜትሮች ርቆ ሌላ የጋ በዓል ይካሄድ ነበር። እዚህ ያሉት ሕፃናትም ነርሷ ቤት እንዳሉት ልጆች በጣም ደስተኞችና ግዴለሾች ናቸው።

ግብዣው ግን የተለየ ነበር። እዚያ የነበረው በብርትኳን፣ በለውዝ እና ጣፋጭ ምግቦች ፋንታ፣ የቾኮላት ብስኩቶች፣ የተለያዩ የአካባቢው ምግቦችና ትልቅ የገና ኬክ ነበር። የልጆቹ ልብስ የጠቆረና ድሪቶ ሳይሆን፣ ብሩህ ቀለም ያላቸው ቀሚሶችና ሹራቦች ናቸው። ሴቶቹ ልጆቹ ፀጉራቸውን በአዲስ ሪቫን ወይም የጨርቅ ጥብጣብ አሥረዋል። ግብዣው የተሟላ ቢሆንም፣ የሻይ ግብዣ እና ልዩ ልዩ ጫወታዎች ሲያበቁ፣ እንዲሁም ደስተኞች ሕፃናት የገና መዝሙር ለማዜም በገናው ዛፍ ዙሪያ ሲሰበሰቡ፣ በስፍራው የነበሩት ትላልቅ ሰዎች ሁሉ አዘኑ፤ ከሁሉም ይልቅ በጣም የምታሳዝነው የዘጠኝ ዓመት ዕድሜ ያላት ተጋባዥ ልጅ ናት።

ስፍራው የዓይነ ሥውራን ትምህርት ቤት ነበር። ብሩህ ፈገግታ ያላቸው ትንንሽ መዘምራን የገናውን ዛፍ፣ ሻማዎቹን ወይም የተሰጧቸውን አሻንጉሊቶች ሊያዩዋቸው አይችሉም። ምግባቸውን በደስታ ተመግበዋል፣ ሙዚቃውን እየተከተሉም ጨፍረዋል፣ አሁን ደግሞ ከልባቸው በመዘመር ላይ ናቸው። ጄኒ የተባለችውና



ከወላጆቿ ጋር የተቀመጠችው ልጅ ግን በጣም አዝናለች። ሁልጊዜ በዓይነ ሥውርነት ጨለማ ውስጥ የምትኖር ቢሆን ደስተኛ እንደማትሆን እርግጠኛ ነበረች። ዓይኖቿን ለጥቂት ጊዜ ካድና ዕውርነት ምን እንደሚመስል ለማሰብ ሞከረች። ማሰቡ እንኳን እጅግ አስቃቂ ነው። ስለዚህ ቶሎ ዓይኖቿን ገለጠችና ሕፃናቱን አየቻቸው።

ጄኒ ራሷ ትምህርት ቤት የተማረቻቸውን የገና መዝሙር በመዘመር ላይ ነበሩ። መዝሙሩ እንዲህ ይላል:-

*አስደናቂው ኮከብ የብርሃን ኮከብ፣*

*ንጉሣዊ ብሩህ ውበት ያለህ ኮከብ፣*

*ወደ ምዕራብ የምትመራ፣ አሁንም የምትጓዝ፣*

*ፍጹም ወደ ሆነው ብርሃንህ ምራን።*

ጄኒ፣ ልጆቹ እንዲህ ያሉትን ቃላት እንዲማሩ የተደረጉት ለምንድን ነው? ብላ ራሷን ጠየቀች። ዕድሜያቸውን ሙሉ በጨለማ የመኖር ዕድል ገጥሟቸው ሳለ ስለ ፍጹም ብርሃን መዘመሩ ምን ይጠቅማል? ነገር ግን ከምትመለከታቸው ሕፃናት ደስተኛ ያልሆነ ልጅ የሌለ መሆኑን ለመቀበል ተገደደች።

የገናን መዝሙርን ታሪክ ጄኒ ታውቃለች። እነርሱም የገና በዓሉ የሚከበርበትን ክፍል ለማስዋቢያነት የተጠቀሙት ውብ በሆነው የገና ታሪክ ሥዕል ነው። መምህራቸው በደማቅ ቀለም የተሠሩትን ሥዕሎች ግድግዳው ላይ አጣብቋቸዋል። ሦስት የሚጓዙ ግመሎች፣ ረጃጅም እና ነጫጭ ፂም ያላቸው ጠቢባን ሰዎች፣ እንዲሁም ለስጦታ የያዙት ወርቅ፣ ዕጣንና ከርቤም በሥዕሉ ላይ ይታያሉ። የሚያበራ ኮከብ ትንሽ ጎጆ ውስጥ ተቀምጣ ሕፃን ልጇን በምታጫውት ድሀ ሴት ላይ ብርሃኑን ፈንጥቆ ይታያል።

እናቷ ነካ ስታደርጋት ጄኒ ከአሳቧ ነቃችና ዓይነ ሥውር የሆኑት ሕፃናት ደስተኛ መሆኗን እንዲያውቁላት በጣም ታጨበጭብ ጀመር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ መዝሙሩ አበቃ። ልጆቹ እንግዶቹን በደስታ ስሜት በመዳሰስ ለማሰናበት ስብስብ አሉ።

እነርሱ እንግዶቹን ሲያሰናብቱ፣ በጣም ትንንሾቹ ሕፃናት ደስ እንዳላቸው ወደ መኝታቸው በእቅፍ ተወሰዱ:: ትልልቆቹ ልጆች ግን በሩ ላይ ስብስብ ብለው በጫጫታና እጃቸውን በማወዛወዝ በየመኪናቸው የሚገቡትን ሰዎች ሲያሰናብቱ ቆዩ:: ያን ጊዜ ነበር ጄኒ ለመጨረሻ ጊዜ ያየቻቸው::

ወደ ቤቷ በምትንዝበት ጊዜ ዝም ብላ ነበር:: ዝም ያለችው ስለ ደከማት ነው ብላ በማሰብ፣ እናቷ በፍጥነት ወደ መኝታ ክፍሏ ወስዳት፣ የጋዝ ማሞቂያውን ለኩሳችና አልጋዋ ላይ እንድታርፍ አደረገቻት:: ጄኒ ከዚያ በፊት በጣም ታማ ነበር የሰነበተችው:: ከሦስት ወራት ቆይታ በኋላ ወደ ውጭ ስትወጣ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነው:: እናቷ ጄኒ በእርግጥ መሄድ ትችል ይሆን ብላ አስባ ነበር:: ነገር ግን ጄኒ መሄድ አለብኝ ብላ ነው አብራቸው የተጓዘችው:: አባቷ የዐይነ ሥውራኑ ትምህርት ቤት መማክርት አባል ሆኖ በመመረጡ ነበር ሁሉም በገናው በዓል ላይ እንዲገኙ የተጋበዙት::

ጄኒ ሐምራዊና ሞቃት ብርድ ልብሷ ውስጥ ሆና የመጡላትን የገና ስጦታዎች ሁሉ ተመለከተች:: መጻሕፍት፣ መጫወቻዎች፣ አዲስ የሌሊት ልብስ፣ የወርቅ ማሠሪያ ያለው ትንሽ ሰዓት እና የመንገድ ሻንጣ ናቸው:: ጥሩ የገና በዓል ነበር:: ከሁሉ የሚበልጠው ስጦታ ደግሞ የራሷ የሆነው በጋጣው ውስጥ የነበረው ድንክ ፈረስ ነበር:: ከራሷ ውጭ ስለማንም አስባ የማታውቀው ጄኒ በድንገት በጣም ዕድለኛ ልጅ እንደ ሆነች ተረዳች:: ጄኒ ስለዓይነ ሥውሮቹ ልጆች አሰበች:: መጫዎቻዎች አሏቸው፣ ግን ሊመለከቷቸው አይችሉም:: እንደገናም ምንም አሻንጉሊት የሌሏቸውን፣ ብዙ ጊዜም ምግብ ስለማያገኙት የሞሮኮ ሕፃናትም አሰበች:: አክስቷ ሮዝመሪ ናት አንዳንዶቹን የምትንከባከባቸው:: ቀደም ብላ በጻፈችላት የገና ደብዳቤ ስለ ልጆቹ ገልጻላታለች:: የሰማችው ነገር አዲስና አስገራሚ ነው:: ስለማታውቀው ዓለም ትንሽ ጭላንጭል ያሳያት አስደናቂ ታሪክ ነበር:: እንደ እርሷ ያሉ ትንንሽ ልጆች አሮጌ ጨርቅ ለብሰው ስለ መሄዳቸው፣ ለኑሯቸው ሠርተው ስለሚያገኙት፣ ከቤት ውጭ ብቻቸውን ስለሚያድሩበት፣ ትንንሽ ሕፃናት የሚመገቡት በማጣታቸው



ስለሚታመሙበት ዓለም አወቀች:: ጄኒ ሕፃናትን የምትወድ ብትሆንም፣ የሚገጥሟት ሕፃናት ሁሉ፣ ሞግዚቶቻቸው የሚንከባከቧቸው ስለሆኑ፤ ልታቅፋቸው ብትፈልግም እንኳ አይፈቅዱላትም:: ሌሎቹ ሕፃናት ግን በጣም ድሆች ስለ ሆኑ፣ ምናልባት ሞግዚቶች የሏቸውም:: በመሆኑም፣ እንድታቅፋቸው ይፈቀዱላት ይሆናል::

በጣም አስደናቂው ነገር፣ አክስቷ ሮዝመሪ ታሪካቸውን በደብዳቤ የገለጸችላትን ሕፃናት በቅርብ ጊዜ ውስጥ የምታያቸው መሆኑ ነው:: ከገና አልፎ ከስድስት ሳምንታት በኋላ እርሷና ወላጆቿ አክስቷንና ለምነው አዳሪ የሆኑትን ሕፃናት ለመጎብኘት ወደ ሰሜን አፍሪካ ተራራዎች በሚወስደው ረጅም መንገድ ላይ በመኪና ይጓዛሉ::

ጄኒን ያከማት ዶክተር የፀሐይ ብርሃን ያስፈልጋታል ብሏል:: ብዙ መድኃኒቶች ወስዳለች፣ ክሬሞች ተቀብታለች፣ ፈሳሾቹንም ጠጥታለች፣ በመኪናም ወጣ ብላለች:: ነገር ግን በታኅሣሥ ወር እንግሊዝ ውስጥ የምትሞቅ ፀሐይ አትገኝም:: ለዚህ ነው ጄኒ የጠራ ሰማይ እና ወርቅማ የባሕር ዳርቻ ወዳለበት፣ ጠንካራ ሆና እንድታድግ፣ ንጣቷ ወደ ቅላት ያደላ፣ እንዲሁም ጤነኛ ወደምትሆንበት ወደ ደቡብ የምትወሰደው::

አባቷ መንገዱን እንዴት ያውቀዋል? በእንቅልፍ ልቧ አሰበች:: በኮከብ እንደ ተመሩት ጠቢባን ሰዎች እነርሱም ፀሐይዋን እየተከተሉ እንደ ሆነ ገመተች:: እናቷ የሚጠጣ ነገርና ብስኩት በትሪ ይዛ ስትመለስ ጄኒን ያገኘቻት ከባድ እንቅልፍ ወስዷት ነው:: ቆማ የልጇን የሚያበራ ፊት እና የተዘናፈለ ፀጉር ለጥቂት ጊዜ ከተመለከተች በኋላ፣ መብራቱን አጥፍታና ትልቁን መስኮት ከፍታ፣ ጄኒ ስለ ከዋክብቱ፣ ስለ ፀሐይ ብርሃን እና የገና ዛፍ እንድታልም ትታት ወጣች::

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት

# በዓሉ ተጀመረ



በመጋቢት ወር አንድ ቀን በማለዳ እንግሊዛዊቱ ሴት ከእንቅልፏ ነቃችና፣ የአየሩን ሁኔታ ለማየት ጠፍጣፋ ወደ ሆነው የቤቷ ጣራ ወጣች:: ጥሩ ቀን ስለ ሆነ ደስ አላት:: እንዲያ እንዲሆን ለረጅም ጊዜ የምትጠብቀው ቀን ነበር:: ከእንግሊዝ የምትመጣው የአጎቷ ልጅ እዚያ የምትደርሰው ያን ዕለት ነበር:: ባሏም ጂኒን ይዟት ይመጣል::

እንግሊዛዊቷን ነርስ በጣም ያስደሰታት የጂኒ መምጣት ነበር:: ወለሉ ላይ እንደ ኳስ ድብልብል ብላ የተኛቸውን ኪንዛን ቀሰቀሰቻት:: ድመቷም አብራት ተኝታ ነበር:: ኪንዛ ከእንቅልፏ በምትነቃበት ጊዜ ሁሉ የምታደርገው የመጀመሪያ ነገር ድመቷ አጠገቧ መኖሯን ለማረጋገጥ እጇን ዘርግታ መዳሰስ ነበር:: ካጣቻት በጣም ትነጫነጫለች:: በዛሬው ማለዳ ግን ማንኛውም ነገር ጥሩ ነበር::

እንግሊዛዊቷ ነርስ እና ኪንዛ እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደ ጣራው ከወጡ በኋላ አንድ ክብ ጠረጴዛ አጠገብ በመቀመጥ ቁርሳቸውን ይበሉ ጀመር::

«ትንሿ ልጅ ዛሬ ትመጣለች:: ሽርሽር እንሄዳለን:: አንቺና እኔ ወደ ገበያ እንሄድና ጥሩ ጥሩ የሚበላ ነገር እንገዛና ለትንሿ ልጅ ግብዣ እናዘጋጃለን፣» አለች ነርሷ ቤት እያጸዳዳች:: ቆሻሻው ኪንዛና ድመቷ ላይ እንዳይበተን ትጠነቀቅ ነበር::

«ግብዣ! ግብዣ! ሳጠራውን እኔ እዝልሻለሁ፤ አሁን እንሂድ፣» አለች ኪንዛ እንደ ፍየል እየዘለለችና ቆሻሻ ማጠራቀሚያው ሳጠራ ላይ እየወደቀች::

«እሺ፣ እንሂድ፣» አለች ነርሷ:: ወዲያው እጅ ለእጅ ተያያዙና ጉዟቸውን ቀጠሉ:: ነርሷ በሳምንቱ መጨረሻ በሚደረገው እረፍት ለሽርሽር ወጣ ካለች ብዙ ጊዜዋ ነው:: በጠዋቱ ክፍለ ጊዜ ከቤት አትወጣም ነበር:: ዛሬ ግን ሰዎች ወደ እርሷ እንዳይመጡ ነግራቸዋለች:: ጂኒን ለመቀበል እንድትዘጋጅ ነፃ ጊዜ ይኖራታል:: በዚሁ መሠረት አበባ ለመቅጠፍ ገና በጠዋት ከተራራው ጀርባ ወዳላው ተራራ ልትሄድ ነው:: አበባው የሚቀጠፍበት ስፍራ ለኪንዛ ስለሚርቅባት፣ ከገበያው የሚገዙትን ነገር ካበቁ በኋላ፣ ቦምቦሊኖ መሰል ምግብ የሚዘጋጅበት ቤት ደረጃ ላይ በማስቀመጥ ሀሚድ እንዲጠብቃት ተወችለት:: ሥራ በሚበዛባት ጊዜ ሁሉ እንዲህ ነው የምታደርገው:: ሁለቱ ልጆች እኅትና ወንድም ሳይሆኑ አይቀሩም የሚል እርግጠኛነት ስላደረባት፣ የጋራ ጊዜ እንዲኖራቸው አስባ ነው ለብቻ የምትተዋቸው:: ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ልብሷ ቆሽሾ እራት ለመብላት ብዙ ባትጓጓም፣ ኪንዛ ሀሚድ በሚጠብቃት ጊዜ ሁሉ ፍጹም ደኅንነት የሚሰማትና ደስተኛ ናት:: ቦምቦሊኖ በጣም ስለምትወድ የተሰጣትን ሁሉ ትበላ ነበር::

ነርሷ ብቻዋን ስትሆን ጊዜ፣ ወደ ተራራው በሚያመራው አሮጌ መንገድ ላይ የመሮጥ ያህል ትራመድ ጀመር:: ከከተማይቱ ዳር ባሉት ያዘመሙ ጎጆዎች በኩል አልፋ በፈረሰው ግድግዳ በር በመውጣት ወደ ተራራው አመራች:: በቅርብ ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ዕድሜ ያላት ሴት የምትሆን መሆኗን ረሳችው:: ወጣትነትም ተሰማት:: ስፍራው እንደ ደረሰችም በዙሪያዋ ያሉትን እምቡጥ አበባዎች መቅጠፍ ጀመረች::

«አበቦቹ እንዴት ያምራሉ! ጄኒን ይዣት እመጣና ከእርሷ ጋር አብረን እንቀጥፋቸዋለን፣» አለች በአሳቧ።

ስለ ጄኒ ባሰበች ጊዜ፣ «ከእርሷና አብረዋት ከሚመጡት ሰዎች ጋር እንዴት ነው አብረን የምንቆየው?» የሚል ሥጋት አደረባት። ሕይወታቸው በጣም ይለያያል። የቤተሰቡ ልጆች አብረው ያድጉ በነበረ ጊዜ፣ እርሷና ኤልሳቤጥ እንደ እኅትማማች ነበሩ። ኤልሳቤጥን አንድ ሀብታም ሰውዬ አገባትና ወደሚያምረው ቤቱ ወሰዳት። ጄኒ ያደገችው በሚያምር አካባቢና በሰላም ነው። በገንዘብና በፍቅር ሊገኝ የሚችል ነገር ሁሉ ነበራት። አክስት ሮዝመሪም ከእነርሱ ጋር ለመኖር ትችል ነበር። ነገር ግን የነርስነት ሥልጠና በምትወስድበት ጊዜ፣ ወደ አፍሪካ ሄዳ ሰዎችን እንድትረዳ፣ ድሆችን እና ጨርቅ ለባሽ ሕፃናትን እንድትንከባከብ እግዚአብሔር ፈለጋት። ኤልሳቤጥና ባሏ አክስት ሮዝመሪ የምታደርገው ነገር የሞኝነት ሥራ ስለሚመስላቸው፣ ስለዚህ ለእነርሱ ደብዳቤ መጻፉና ስለ ሕይወቷ መንገር ያስቸግራት ነበር።

እነርሱ የሚጽፉት ደብዳቤ ሁሉ በዋናነት ስለ ጄኒ ነበር። ገና በመጣ ቁጥር ኤልሳቤጥ ፎቶግራፏን ለሮዝመሪ ስለምትልክላት፣ በአስተዳደጓ ቅደም ተከተል ፎቶውን ማኅደር (አልበም) ውስጥ ታከማች ነበር። የመጨረሻው የጄኒ ፎቶግራፍ ድንክዬ ፈረስ ላይ ተቀምጣ የተነሣችው ነው። ሮዝመሪ ይህን አሰበችና ጄኒ በምትመጣበት ጊዜ የሙሪሽ ሕፃናት የሚጫወቱባቸውን ተራ አሻንጉሊቶች አይታ ምን ይሰማት ይሆን ብላ አሰበች። ጄኒ ውድ በሆኑ አሻንጉሊቶች ስትጫወት፣ ጥሩ ልብስ ስትለብስና አባቷ መሬት ላይ በድንክዬ ፈረስ ስትጋልብ ነው የኖረችው። በምትመጣበት ጊዜ ምናልባት ነገሩ ሁሉ ያስጠላት ይሆናል። ሮዝመሪ እነዚህን ሁሉ እያሰበችና ኀዘን እየተሰማት፣ አበቦቹን ይዛ በፍጥነት ከተራራው ወረደች። ከዚያም ኪንዛን ይዛ ወደ ቤቷ ሄደች።

መጫወቻ ወደሚከማችበት ቁም ሳጥን ሄዳ ያሉትን ነገሮች በኀዘን ስሜት መረመረቻቸው። ያሉት የቆሸሹና የተቀደዱ መጻሕፍት፣ ቀለማቸው የለቀቀ ተገጣጣሚ የሥዕል እንቆቅልሾች፣



የተጠረቡ ጡቦች፣ የተጨማደዱ ትንንሽ አሻንጉሊቶች እና አንድ ትንሽ ሳጥን ውስጥ የተከተቱ የጠመኔ (የቾክ) ስብርባሪዎች ብቻ ናቸው። እነዚህ ሁሉ አሻንጉሊት አይተው በማያውቁ ልጆች የተወደዱ ነበሩ፣ አሁን ግን አርጅተዋል። አክስት ሮዝመሪ በረጅሙ ተንፍሳ ቁም ሳጥኑን ከዘጋች በኋላ፣ ኬክ ለመጋገር ወደ ወጥ ቤት ሄደች።

ከቀኑ አሥር ሰዓት ተኩል ሲሆን፣ ትንሹ ቤት በጥሩ ሁኔታ ፀድቶ ብሩህ ሆኗል። ሳሎኑ ከጫካ በተለቀሙ የአበባዎች መዓዛ ተሞልቷል። ሻይ ተዘጋጅቷል። የሻይ ጀበናው በምድጃው ላይ የሚዘምር ይመስላል። አክስት ሮዝመሪ እና ኪንዛ ሆቴሉ በር ላይ የቆመውን መኪና ለማግኘት ወጥተው ሄዱ።

መኪናው የደረሰው በትክክለኛው ሰዓት ነበር። የሚያምር መኪና ነበር። ትንንሾቹ ልጆች የከበቡት ቀድመው ሻንጣ ለመሸከም እርስ በርሳቸው ይደባደቡ ጀመር። አክስት ሮዝመሪ የመጡት እንግዶች ከመኪናው እስኪወርዱ ቆማ ጠበቀች። ወዲያው በሕፃናት ትርምስ መሀል፣ «እያት፣ እማዬ! እንዴት የምታምር ልጅ ናት! አክስት ሮዝመሪ ትንሽ ልጅ እንዳለቻት አልነገርሽኝም፣» የሚል የልጅ ድምጽ ሰማች።

እንግዶቹ ከልጆቹ ጫጫታና ትርምስ መሀል ወጡ። ኤልሳቤጥ፣ ከአሥር ዓመት በፊት እንደ ነበረችው አሁንም ልጅ እግር ናት። የአክስቷን ልጅ ሮዝመሪን እቅፍ አድርጋ ትስማት ጀመር። ጄኒ ኪንዛን ለማነጋገር እና ራሷን ለማስተዋወቅ አጠገቧ ቁጢጥ ብላለች።

«ጄኒ አክስት ሮዝመሪን አልሳምሻትም እኮ፣» አለች እናቷ ቆጣ ባለ ድምፅ።

ጄኒ ብድግ ብላ በትሕትና አክስቷን ከሳመች በኋላ ወደ ኪንዛ ተመለሰች። ትልልቆቹ ሰዎች ሻንጣዎችን፣ ፓስፖርቶችን እና የሚጻፉ ፎርሞችን ሲያሰባስቡ፣ ሮዝመሪ ልታያት ለብዙ ጊዜ ስትመኝት የነበረችውን ልጅ ቆማ ትመለከታት ነበር። በአሳቧ፣ ደስ የምትል ትንሽ ነገር እያለች ልትተዋወቃት ሄደች።

ጂኒ ግን አክስቷን የተመለከተቻት ግራ በተጋባ አስተያየት ነበር::

«ይህቺ ትንሽ ልጅ ምን ሆናለች? ደስ የሚለውን የልብስ ጌጤን ላሳያት ብሞክርም፣ ወደ እኔ ከማየት ይልቅ ፊት የምትመለከተው፣ ለፊት ነው» አለች::

«ዐይነ ሥውር ናት ጂኒ፣» አለች አክስት ሮዝመሪ በእርጋታ:: ቀጥላም፣ «እንዲያ ስለሆነች ግን አብረሻት ልትጫወቺ አትችይም ማለት አይደለም:: የምትዳስሰው መጫወቻ ልትሰጫትና መዝሙር ልትዘምሪላት ትችያለሽ:: ትዳስስሽ:: ቶሎ ትወድሻለች፣» አለቻት::

ከዚያም የኪንዛን ትንሽ እጅ ያዝ አድርጋ፣ የጂኒን ፊት እና ፀጉር አስዳሰሰቻትና፣ «እንዲህ ነው ሰዎችን የምታውቃቸው፣» አለች:: ይህን ብላ የጂኒን እናትና አባት ለማናገር ዘወር አለች:: ይሁን እንጂ፣ አንዳች ነገር ከመናገሯ በፊት፣ ጂኒ የእናቷን እጅ በመያዝ  አንጋጣ አየቻት:: እንባ በዓይኖቿ ግጥም እያለ:-

«እማዬ፣ ልጅቱ ዐይነ ሥውር ናት፣ ልክ እንደ ትንንሾቹ የገና ልጆች፣» አለች በሹክሹክታ::

«ምንም አይደለም:: በጣም ደስተኛ ትንሽ ልጅ ነው የምትመስለው:: አንድ ትንሽ ስጦታ ልንፈልግላት ይገባል:: አሁን ግን እንሂድና የአክስት ሮዝመሪን ቤት እንይ፣» አለች የጂኒ እናት ወይዘሮ ስዊፍት በርጋታ:: ገበያውን እያቋረጡ ጉዞ ጀመሩ:: ትልልቆቹ ከፊት ቀደሙ:: ጂኒ ደግሞ ኪንዛን እየመራቻት ከኋላ ተከተሏቸው:: ጂኒ በአዲሷ ጓደኛዋ በኪንዛ ሁኔታ ስለ ተማረከች፣ በዙሪያዋ ያለውን የከተማ ሁኔታ ልብ ብላ አላየችም:: በእረፍት ጉዟቸው ወቅት ከነበራት ጊዜ ሁሉ ይበልጥ ደስተኛ ሆናለች:: እናትና አባቷን በጣም የመውደዷን ያህል የዘጠኝ ዓመት ስለ ሆነች አብሯት የሚጫወት ልጅ ትፈልግ ነበር:: ከሁሉም ይልቅ የምትንከባከበው ልጅ ትፈልጋለች:: በአሻንጉሊት ከመጫወት አልፋለች:: ለማዳ እንስሳዎቿም ቤት ስለ ቀሩ በጣም ናፍቃቸዋለች:: ጥቁር ሉጫ ፀጉር ያላት የሦስት ዓመት ዐይነ ሥውር ልጅ ግን ከለማዳ እንስሳትም በጣም ትሻላለች:: እንዲህ



ስላለ አስደሳች ነገር አልማም አታውቅ::

አክስት ሮዝመሪ እምትኖርበት አካባቢ ካለው ጠባብ የመንደር መንገድ ደርሰዋል:: ወይዘሮ ስዊፍት በምታልፍበት መንገድ ላይ የተቀመጡትን ችግረኛ ሕፃናት ላለመመልከት ትሞክራለች:: በበር ላይ የሚለፈልፈው ሽማግሌ ሁኔታም አስጨንቋታል:: ከሮዝመሪ ጋር የምትነጋገረው በፍርሀት ነው:: ከተማው ዳር ካለ አንድ ቤት በር ላይ ደርሰው፣ አክስት ሮዝመሪ መክፈቻ ቁልፍ ከቦርሳዋ ስታወጣ ባየቻት ጊዜ ደግሞ ይበልጥ ደነገጠች:: በለበሰችው ጨርቅ የተጠቀለለ ነገር ወደ ጡቷ አስጠግታ ያቀፈች አንድ ድሃ ሴት በሩ ላይ ተቀምጣለች::

ሮዝመሪ በምታነጋግራት ጊዜ ሴትዮይቱ የጠቀለለችበትን ጨርቅ ገለጠችና በበሽታና በድካም የጠወለገ እጅግ ከሲታ ሕፃን አሳየቻት:: ወይዘሮ ስዊፍት በተመለከተችው ነገር ደንግጣ ጂኒን ልትይዛት እጇን ብትዘረጋ አጣቻት:: ከሮዝመሪ ጋር ወደ ፊት ቀድማ በመሄድ አሳዛኙ ሕፃን አጠገብ ተንበርክከው በመገረም ይመለከቱታል::

«ጂኒ! ነይ ወዲህ!» አለች እናቷ:: ጂኒ ግን ለእናቷ ጥሪ ትኩረት አልሰጠችም:: በድንጋጤ ሮዝመሪን እያየች፣ «ሊሞት ነው?» አለች::

«እንጃ፣ እንደማይሞት ተስፋ አደርጋለሁ፤ ወደ ቤት እንግባ፣» አለች ሮዝመሪ:: የፊት ለፊቱን በር በመክፈት ሕፃን ያቀፈችውን ሴት ወደ መድኃኒት መስጫው ክፍል ወስዳ አስቀመጠቻትና ወደ እንግዶቿ ተመለሰች:: ወይዘሮ ስዊፍት ሮዝመሪ በር ላይ የተቀመጠችውን አሳዛኝ ሴት በመመልከቷ ከድንጋጤው እያንሠራራች እንደ ቆመች ናት:: ወጣት የሆነችው የሕፃኗ እናት፣ መከራ የበዛባት እና በሽተኛነትን የሚገልጥ ፊት እንዳላት ተመለከተች:: ልጇን ለነርሷ በምታሳያት ጊዜ በሚያምሩ ዓይኖቿ ውስጥ ተስፋ ይገለጥ ነበር::

«ሮዝመሪ፣ ስለ እኛ አትጨነቂ፤ ራሳችንን እናስተናግዳለን:: ሂጂና ለዚያ ደሀ  ሕፃን የሚያስፈልገውን ነገር አድርጊለት፣» አለች

ወይዘሮ ስዊፍት።

አክስት ሮዝመሪ አሰብ አደረገችና። «እሺ፣ ወደ ፎቅ እንውጣና ሳሎኑን ላሳያችሁ። ሻይ በመፍላት ላይ ነው፣» አለች።

እንዲያ ባለ ቆሻሻ መንገድ አልፎ በአበቦችና በሥዕሎች ባማረ፣ እንዲሁም ጣፋጭ ምግብ የተደረደረበት ጠረጴዛ አለበት ብሩህ ክፍል ውስጥ መግባት አስደናቂ ነገር ነበር። አክስት ሮዝመሪ እንግዶቹ ወለሉ ላይ በተዘጋጀው ፍራሽ ላይ እንዲቀመጡ ካደረገች በኋላ፣ ሻይ አቀረበችላቸውና፣ «ነገሩ ተገቢ ባይመስልም፣ ለአምስት ደቂቃ ያህል ለብቻችሁ እንድተዋችሁ ትፈቅዱልኛላችሁ? ያያችኋትን ሴትዮ አውቃታለሁ፤ አራት ልጆች ሞተውባታል፤ ያቀፈችው ልጅ ብቻ ነው የቀራት፣» አለች ኀዘኔታ በሞላበት አነጋገር።

ጄኒ የአክስቷን እጅ ያዝ አደረገችና፣ «መጥቼ አግዝሻለሁ፣» አለች።

«አይቻልም ጄኒ፣ እንዲህ ያለው ነገር በፍጹም አይደረግም። ቁጭ በይና ሻይሽን ጠጪ፣» አለች እናቷ ቆጣ ብላ።

«እምቢየው እሄዳለሁ! ሕፃኑ ድኖ ሳየው እፈልጋለሁ። ምንም ሻይ አልፈልግም! ለመሄድ እንደምችል ተናገረ በኀዘኔታ ስሜት።

የጄኒ አባት ብድግ ብሎ እጇን ያዝ አደረጋትና፣ «ምን ሆነሻል ጄኒ?» ካለ በኋላ ሮዝመሪን እያየ፣ «በሽታው ወደ ሌላ ሰው ይተ ላለፋል?» አለ

«አይመስለኝም። ከዚህ ቀደምም አይቼዋለሁ። የረሀብና ያልተ ስተካከለ አመጋገብ ሥቃይ ነው፣» አለች ሮዝመሪ።

«ኤልሳቤጥ፣ ሮዝመሪ ግድ ከሌላት እንድትሄድ ልፍቀድላት አለ፣» የጄኒ አባት ሚስቱን እያየ። ጄኒ በአሸናፊነት ስሜት ከክፍሉ ስትወጣ፣ እርሱ ወደ ሚስቱ ተመለሰና፣ «የምትችለውን ሁሉ በማድረግ አክስቷን ትርዳ። አንድ ሰው መርዳት አለባት። እንዲህ ያለውን ነገር ማየት ራስ ወዳድነቷን ይቀንሰዋል። እርግጠኛ ነኝ፣ ሮዝመሪም ብትሆን ለተላላፊ በሽታ ጥንቃቄ ታደርጋለች፣» አለ።



የጄኒ እናት በረጅሙ ተነፈሰችና፣ «ይሆናል፣ ታናናሽ ወንድሞችና እኅቶች ቢኖሯት ጥሩ ነበር፣» አለች ምኞትን በሚገልጥ አነጋገር።

በዚህ ጊዜ ጄኒ እና አክስቷ ጎንበስ ብለው ፊቱ በረሀብ የነጣውን ሕፃን ይመለከቱ ነበር። እናቱ በተለመደው ሁኔታ ስለ ድህነት፣ ድንቁርና እና ስለተሳሳተ አመጋገብ ትነግራቸዋለች። ሕፃኑን ለማዳን የማይቻል ቢመስልም፣ አንድ ዕድል ግን ነበር። አክስት ሮዝመሪ ሕፃኑን በብርድ ልብስ እየጠቀለለች ወደ ጄኒ መለስ አለችና:-

«ወደ ፎቅ ወጥተሽ ኩባያ፣ ማንኪያና ትንሽ ስኳር አምጪልኝ። ከምድጃው በላይ አለው መደርደሪያ ላይ አለ፣» አለች። ጄኒ የታዘዘችውን በፍጥነት ፈጸመች።

«አሁን ደግሞ ሂጂና ማንቆርቆሪያውን አምጪልኝ፣» አለቻት አክስቷ። በፍጥነት እሮጠች ጄኒ።

«አሁን ደግሞ እዚያ ሦስተኛው መደርደሪያ ላይ ያሉትን ኪኒኖች አምጪልኝ፣» አለች አክስቷ ቆጣ ብላ። ጄኒ የአክስቷ ንግግር ደስ አላላትም።

«አሁን ደግሞ እባክሽ ያን ኩባያና ማንኪያ በዚያ በፈላ ውኃ እጠቢው . . . አንዱን ክኒን ስበሪው. . . በትንሽ ውኃ በጥብጪው. . . ያን ጠርሙስ ስጪኝ. . » አለች አክስት ሮዝመሪ።

ጄኒ ቁጣዋን፣ አክስቷን እና እራሷን ረሳች። ሕፃኑ መድኃኒቱን በሚጠጣበት ጊዜ ከጉሮሮው የሚሰማውን ደካማ ድምፅ እየሰማች በዝምታ ምንጣፉ ላይ ተንበርክካለች። ጠብ ጠብ እያለ መድኃኒቱ በሕፃኑ ጉሮሮ ወረደ። ከዚያም ሮዝመሪ ጣፋጭነት ያለው ውኃ በተደጋጋሚ በማንኪያ አጠጣችውና እናቱን በአረብኛ አናገረቻት። ሕፃኑን አቅፋ ለአንድ ሰዓት በጸጥታ መቀመጥ የሚያስፈልጋት መሆኑን እና ከዚያ በኋላ ለሕፃኑ እንደገና የሚጠጣ መድኃኒት እንደምትሰጣት ገለጸችላት።

«ሊሻለው ይገባል፣ ሊሻለው ይገባል!» አለች ጄኒ በአሳቧ።

ከዚህ በኋላ አክስት ሮዝመሪ ጄኒን ያስደነቃት አንድ ነገር አደረገች፡፡ ኢየሱስ አንድ ሕፃን አቅፎ ወደሚታይበትና ግድግዳው ላይ ወደ አለው ሥዕል እያመለከተች፣ ታሪኩን ለሴትየዋ ከነገረቻት በኋላ ድምጿን ከፍ አድርጋ ለበሽተኛው ሕፃን ጸለየችለት፡፡


ጄኒ አክስቷ የምትለው ነገር ባይገባትም፣ በመጸለይ ላይ መሆኗን ግን አውቃለች፡፡ ጸሎቱ የሚያደርገው ጥሩ ነገር ይኖራል ወይ? ብላ እያሰበች እርሷም ግድግዳው ላይ ያለውን ሥዕል አየት አደረገችው፡፡ ሥዕሉ ላይ በእቅፉ ያለው ልጅ ሁኔታ እናቱ ላቀፈችው እውነተኛ ሕፃን የሚያስተማምን ነገር ያለው አስመሰለው፡፡

«ቶሎ እንደሚሻለው እርግጠኛ ነኝ፣» አለች ጄኒ እንደገና ወደ ሕፃኑ ጎንበስ ብላ፡፡ እንደዚያ እየተመለከተችው ሕፃኑ ደካማ ሽፋኖቹን ቀስ በቀስ ሰበሰበና ዓይኖቹን ገለጣቸው፡፡



## *ምዕራፍ አሥራ አራት*

# ብርሃን መብራት ጀመረ



ወደ እንግሊዝ የመመለሻ ጊዜያቸው እስኪደርስ፣ እዚያው መቆየት እንደሚኖባቸው እና እርሷም እስከዚያው የኪንዛ ተንከባካቢ እንደምትሆን፣ እንዲሁም ክሊኒኩ ውስጥ ያሉትን ሕፃናት በማከም ሥራ አክስት ሮዝመሪን የምትረዳት መሆኗን ጄኒ ስለ ወሰነች፣ ቤተሰቦቿ ሌላ ዕቅድ ማውጣት አላስፈለጋቸውም፡፡

የጄኒ አባት ሳቀና፣ ሁለት ሳምንት ሙሉ በተራራማው የገጠር መንደር ውስጥ ምን እየሠራ እንደሚቆይ አሰበ፡፡ እናቷ ወይዘሮ ስዊፍት ደግሞ በሥጋት ተነፈሰችና ጄኒ በቀን ሦስት ጊዜ አፏን መጉመጥመጥ አለባት ብላ ወሰነች፡፡ ጄኒ ደስተኛነቷን በግልጽ ታሳይ ነበር፡፡ ሮዝመሪም አልተናገረችም እንጂ በጣም ደስ ብሏታል፡፡ የእንግዶቿ የእረፍት ጊዜ የተሳካ እንደሚሆን ተሰማት፡፡

ዕለቱ እሑድ ከሰዓት በኋላ ነበር፡፡ እሑድ ዕለት ወደ ክሊኒክ የሚመጣ ሰው ስላልነበረ፣ የሴቶች ስብሰባ ተካሂዶ ነበር፡፡ ከስብሰባው እየወጡ ወደየቤታቸው የሚሄዱት ሴቶች፣ ልጆቻቸውን ጀርባቸው ላይ ጥብቅ በማድረግ ከራስ እስከ እግር ጥፍር በሚሸፍናቸው ነጭ ቀሚሳቸው ውስጥ እያዘሉ ሲጓዙ ጄኒ ታያቸው ነበር፡፡

«ልጆቻቸውን እንደዚያ አዝለው ሲታዩ፣ ባለ ሻኛ ግመል ይመስላሉ። ሕፃናቱ ይታፈናሉ ብላችሁ ታስቡ ይሆናል፣ አታስቡም? ለምንድን ነው እንደ ሌላው ሰው የሕፃናት ጋሪ የማይኖራቸው?» አለች ጄኒ አክስቷን እየተመለከተች።

«የሕፃናት ጋሪ ለመግዛት አይችሉም። እንዲህ ሲታዘሉ ለሕፃናት ጥሩ አይደለም። ብዙ ልጆች ንጹሕ አየር ለማግኘት ስለማይችሉ የመተንፈሻ አካላቸው ደካማ ይሆናል። አንዳንዶቹ እንዴት እንደ ገረጡ አይተሻል፣» አለች አክስት ሮዝመሪ በፈገግታ።

«ቡራቡሬ፣ ቀጫጫና እድፋምም ናቸው። ልጆቻቸውን በጥሩ ሁኔታ ማሳደግ ያለባቸው መሆኑን እንደ አንቺ የሚያስተምራቸው ሌሎች ሰዎች አለመኖራቸው ያሳዝናል። አየሽ አክስቴ፣ እስከ ዛሬ ሳስብ ነበር፣ ሳድግ እንዳንቺ ሚሲዮናዊ ለመሆን ወስኛለሁ። ወደዚህ መጥቼ ክሊኒክ በመክፈት፣ አንቺ እንደምታደርጊው ብዙ ሰ ዎችን አክማለሁ። ደስ የሚል አገልግሎት እንደሚሆን አስባለሁ።»

አክስት ሮዝመሪ፣ እርግጠኛነት የሚታይበትን የጄኒን ፊት ትኩር ብላ በማየት ለትንሽ ጊዜ ዝም ካለች በኋላ፣ «አንድ በጣም ጠቃሚ ነገር በሕይወትሽ ካልተፈጸመ ሚሲዮናዊ ለመሆን አትቺይም ጄኒ፣» አለች።

«ለምን አልችልም አክስቱ? ስለ ነርስነትና ሕፃናትን ስለ መጠበቅ ልማር እችላለሁ። ከዚህ ሌላ ነገር ማወቅ አያስፈልገኝም። ያስፈልገኛል እንዴ?»

«አዎ፣ የሚያስፈልግሽ ይመስለኛል። እርሱን አሁን እዚህ መተ ላላፊያ ላይ ልነግርሽ አልችልም። ወደ መናፈሻው እንሂድና እዚያ ሻይ እየጠጣን እነግርሻለሁ። ኪንዛ ይሄኔ ነቅታ ይሆናል። እርሷም ወደ መናፈሻው መሄድ ትወዳለች፣» አለች ሳቅ እያለች።

«እንዴት በጣም ደስ የሚል ነው!» ብላ ጮኸች ጄኒ። ከዚያ ሁለቱን ደረጃ በአንድ ጊዜ እየተራመደች ወደ ላይኛው ክፍል ለመዘጋጀት ወጣች።



አንቺ ከጋበዝሽኝ ሻይ ለመጠጣት እንድቆይ እማዬ ነግራኛለች። እኔም ጠይቄአታለሁ።

«ጠይቀሻታል? እንግዲያው እኔ ለሽርሽሩ የሚያስፈልገንን ነገር እስካሰናዳ ኪንዛን ታዘጋጂያታለሽ? ከዚያ እንሄዳለን፣» አለች አክስት ሮዝመሪ እየሳቀች።

ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ ሮዝመሪ፣ ጄኒ እና ኪንዛ ኮረብታው አካባቢ ወዳለው መናፈሻ በሚወስደው ደረጃ መውጣት ጀመሩ። አካባቢው በጣም ያምራል። በጸጥታ ቆሙና ለጥቂት ጊዜ ሁሉን ነገር ተመለከቱ።

«ኩሬው ውስጥ እንዳትወድቅ ኪንዛን ያዣት። ተቀምጠን ሻይ የምንጠጣበትን ምንጣፍ እስክዘረጋ ድረስ ጠብቂያት፣» አለች አክስት ሮዝመሪ በማስጠንቀቂያ ዓይነት ንግግር። ለሽርሽር ስፍራ ያዘጋጀቻቸውን ነገሮች ፈታታችና ቁጭ ብላ ሁለቱ ሕፃናት ሲጫወቱ ተመለከተቻቸው። ኪንዛ ጠንካራና ቆንጆ ልጅ ሆና በማደግ ላይ ናት። እርሷ ማን ነበረች? ወደፊትስ ምን ትሆን ይሆን? የወደ ፊት ዕድሏን በተመለከተ ተግባራዊ የሚሆን ዕቅድ ሊወጣላት ይገባል ብላ አሰበች አክስት ሮዝመሪ። ጠቃሚ እና የእጅ ጥበብ እውቀት ያላት ሰው ሆኖ ማደግ የሚኖርባት ከሆነ፣ ይህ ነው መደረግ ያለበት አለች። ጄኒስ፣ ግዴለሽ እና ራስ ወዳድ ሆና ልታድግ ነው? ብላ አሰበችና፣ እንዲያ አይሆንም ብላ ተስፋ አደረገች።

ጄኒ የሽርሽር ስፍራው ምንጣፍ መዘርጋቱን አየችና ኪንዛን ይዛ በፍጥነት መጣች። ኪንዛ ክብ ኬክ ተሰጣት። ጄኒ ደግሞ ሳንድዊች መመገብ ጀመረችና ወደ አክስቷ ዘወር ብላ፣ «ሚስዮናዊ ለመሆን እችል ዘንድ ላውቀው የሚገባ ሌላ ነገር ምንድን ነው?» አለች። ጥያቄዋ ጠንካራና ባልተቋረጠ ውይይት መሀል የሚነሣ ይመስል ነበር።

«ለማድረግ በምትፈልጊው ነገር ላይ ይመሠረታል። የሰዎችን ሕመም ለመፈወስ ብቻ የምትፈልጊ ከሆንሽ፣ ነርስ ወይም ዶክተር ለመሆን መሠልጠን አለብሽ። እዚህ ያሉት ሰዎች ግን በጣም ድሀ

ዎች ስለ ሆኑ እንደገና ወዲያው የሚታመሙ ናቸው:: ያም ሆነ ይህ፣ ከሰውነታችን የትኛውም ክፍል ፍል ዋናው ለዘላለም የሚኖረው ነው:: እውነተኛው ማንነታቸው መንፈስ እያልን የምንጠራው ነው:: ሰዎችን ወደ ጌታ ኢየሱስ በመምራት፣ በእርግጠኛ ሁኔታ ልትረጂያቸውና ደስተኞች ልታደርጊያቸው ትችያለሽ:: አንቺ ራስሽ ክርስቶስን በሚገባ ካላወቅሽው ግን ይህን ለማድረግ አትችይም:: ስለዚህ ዋናው ነገር፣ ምን ማወቅሽ ሳይሆን፣ ማንን ማወቅሽ ነው፣» አለች አክስት ሮዝመሪ ረጋ ብላ::

«አንቺ ለበሽተኞቹ በየቀኑ መድኃኒት እየሰጠሻቸው ይህን ያህል ረጅም ጊዜ አሳልፈሻል:: እኔስ ይህን ለማድረግ የማልችለው ለምንድን ነው?»

«ትቺያለሽ:: እኔ ይህን የማደርገው በሽተኞቹ እንዲሻላቸው ብቻ ሳይሆን:: ኢየሱስ እኔ ውስጥ እንደሚኖር፣ ለበሽተኞቹ እንደሚያስብና ሊፈውሳቸው እንደሚፈልግ እንዲያውቁም ነው:: መልካም ነገሮችን በማድረግ የኢየሱስን ፍቅር ማሳየት ይኖርብሻል:: አሁን እርሱ በምድር ላይ የለም:: ነገር ግን መንፈሱ በሚወዱትና በሚያምኑት ሰዎች ልብ ውስጥ እየኖረ በእነርሱ በኩል ይሠራል:: ስለዚህ፣ በመጀመሪያ እርግጠኛ ልትሆኚበት የሚገባ ነገር፣ ኢየሱስ እውስጥሽ የሚኖር መሆኑን ነው፣ በአንቺ በኩል ሌሎቹን መውደዱን ነው:: ያለዚያ ሥራሽ ባዶ ፋኖስ ወይም ኩራዝ ይዞ ወደ ጨለማ ስፍራ እንደ መሄድ ይቆጠራል::»

«እርሱ እዚያ መኖር አለመኖሩን በምን ታውቂያለሽ?» አለች ጄኒ::

«እንዴት ብርሃን ወደ ባዶው ፋኖስ እንደሚገባ ማለትሽ ነው?» ብላ አክስት ሮዝመሪ ጠየቀች:: :: «በር ከፍቶ ፋኖሱን ቤት ውስጥ የማስቀመጥ ጉዳይ ብቻ ነው:: ኢየሱስ ብርሃን ነው፣ ወደ ውስጥ ለመግባት ይፈልጋል:: የፋኖሱ መስታወት ንጹሕ ከሆነ፣ ብርሃኑ በጣም ቦግ ይላል:: መስታወቱ ጉም የመሰለና ቆሻሻ ከሆነ ግን፣ ብርሃኑ በጣም የደበዘዘ ይሆናል:: ከፈቀድንለት ኢየሱስ ውስጣችንን እንደ መስታወቱ ያጸዳዋል፣ ማለት ቁጡዎች፣ እንዲሁም ትዕ



ግሥት የለሾችና የማንታዘዝ እንዳንሆን በመርዳት እንዲያ ያደርገናል:: ከዚያ በኋላ የኢየሱስ የፍቅር ብርሃን በውስጣችን ስለሚያበራ፣ ሰዎች ወደ እርሱ ይቀርባሉ:: እርሱ ፋኖስ ሳይሆን፣ ብርሃን ነው::»

ለጥቂት ጊዜ በመካከላቸው ዝምታ ሆነ::

«ስለዚህ ሚሲዮናውያን የሚሆኑት ጥሩ ሰዎች ብቻ ናቸው ማለት ነው፣» አለች ጄኒ እያሰላሰለች::

«እንደዚያ አይደለም:: ብዙ ሰዎች አሉ፣ ያለ ኢየሱስ በጣም ጥሩ እና ደግ የሆኑ:: ልክ ወርቃማ ፋኖሶች በፀሐይ ብርሃን ውስጥ ስታስቀምጫቸው እንደሚያበሩት:: በምሽት ጊዜ ፀሐይ ስትጠልቅ ግን ፋኖሶቹ የሚያንጸባርቁት ብርሃንም ይጠፋል:: እንዲሁ የእኛ ጥሩ ሰው መሆን የሚቆየው መሥራት ስንችል ብቻ ነው - እስክንሞት ድረስ:: የኢየሱስ ፍቅር፣ ሕይወት እና መልካምነት ወይም ቸርነት ግን ለዘላለም ይኖራል:: የኢየሱስ ብርሃን ውስጡ ያለበት ሰውም ለዘላለም ይኖራል:: የዘላለም ሕይወት የሚባለው ይህ ነው:: ይህን የመሰለው ጥሩነት ከሌላው ዓይነት ጥሩነት በጣም የተለየና ጠንካራ ነው::»

«እማዬና አባዬ ወደ አትክልቱ ስፍራ መጡ፣» አለች ጄኒ፣ ድንገት የሮዝመሪን ንግግር አቋርጣ ወደ ወላጆቿ እየሮጠች:: ውይይቱ ስለ ተቋረጠላት በጣም ደስ አላት:: አክስት ሮዝመሪ የምትገልጽላት ነገር አስጨንቋታል:: እንዲህ ያለውን አስጨናቂ ነገር አትወድም:: ነገር ግን ምንም ሆነ ምን፣ ሁልጊዜ ለእናት እና ለአባቷ በዓለም ካሉ ነገሮች ሁሉ እጅግ አስፈላጊ ሰው እንደምትሆን ታውቃለች::

አክስት ሮዝመሪ ደካማይቱን ኪንዛን እየመራች ጄኒን ተከተለቻት:: እልፍ እንዳለችም የጄኒን እናት ኤልሳቤጥን አይታ ፈገግ አለች:: ጄኒ እንደገና ጠንካራ ሆና ስትሯሯጥ ማየቱ በጣም ያስደስታል:: ሽርሽሩ ለሁለቱ ሴቶች ካስገኘላቸው በጣም ጥሩ ነገሮች አንዱ፣ የቆየ ወዳጅነታቸው መታደሱ ነው:: የሁለቱ የሕይወት አቅጣጫ የተለያየ መሆኑ ለያይቶ የሚያስቀራቸው

ይመስል ነበር፤ አሁን ግን በፊት እንደ ነበረው ጠንካራና እርግጠኛ እንደ ሆነ ተሰማቸው። አክስቷ ጊዜዋን በከንቱ በማባከን ላይ አለመሆኗን ኤልሳቤጥ አምናለች። ይህን ያስተማራት በሕመምተኛ ሕፃን እናት ፊት ላይ ይታይ የነበረው ሁኔታ ነው። ክሊኒኩ ቁስልና በሽታ አምጪ ጀርሞች ቢኖሩበትም፣ ከዚያ ቀደም ማንንም ባላመነችበት ሁኔታ፣ ልጅዋ ጄኒ ከእርሷ ጋር እንድትሆን ሮዝመሪን አመነቻት። ይህ የኤልሳቤጥ ሁኔታ ያልተለመደ ነበር። ከጥቂት ሳምንታት በፊት ትንሽ ልጇ ከድህነት እና በሽታ ጋር ምን ጉዳይ ይኖራታል የሚለው አሳብ እጅግ ያስፈራት ነበር።

ብዙ ዓይነት ውበቶች አሉ ብላ አሰበች። መፈወስ፣ መርዳት፣ መውደድ እና መስጠት ውብ ነገሮች ናቸው። ጄኒ ጥሩ እና ራስ ወዳድ ሳትሆን እንድታድግልኝ እፈልጋለሁ። ሮዝመሪ እንዲያ እንድትሆን ልትረዳት የምትችል ይመስለኛል።

በኋላ ይህን አሳብ ለባሏ ስትነግረው፣ «ክሊኒኩ ውስጥ ተ ግባራዊ የሆነ ነገር በመማር ላይ ስለ ሆነች፣ ጥሩ ነርስ የምትሆንበት መንገድ ይከፈትላት ይሆናል፣» አለ።

«ሮዝመሪ፣» አለች ኤልሳቤጥ ኪንዛን እቅፍ እያደረገች፣ «ዛሬ ማታ ልጆችሽን ተወት አድርገሽ አረፍንበት ሆቴል ውስጥ አብረሽን ራት ልትበይ አትችይም?» አለቻት።

«እሑድ እሑድ አይመጡም። የእረፍት ቀኔ ነው። ከሰዓት በኋ ላ ብቻ ነው ስብሰባ ያለብኝ። በደስታ እመጣለሁ፣» አለች ሮዝመሪ።

በዚህ ጊዜ ጄኒ ድምጿን ከፍ አደረገችና፣ «እይው እማዬ፣ ፒኮ ክን የኋላ ላባውን ዘረጋው፣» አለች። ወላጆቿም አብረዋት በመሄድ ጣዎሱ (ፒኮኩን) እንዲመለከቱ እያጣደፈቻቸው። በዚህ ጊዜ ሮዝመሪ እና ኪንዛ እያዘገሙ ወደ ቤታቸው አመሩ።

ከአንድ ሰዓት በኋላ ሮዝመሪ ወደ ተጋበዘችበት ሆቴል በመሄድ፣ ከጄኒ እና ከወላጆቿ ጋር ራት መመገብ ጀመረች። ጄኒና ወላጆቿ ሮዝመሪን ለማስተናገድና እንኳን ደህና መጣሽ ለማለት ጥሩ ጥሩ ልብስ ለብሰዋል። ራት መጋበዟ ለሮዝመሪ ትልቅ ነገር ነበር። ከኤልሳቤጥ ጋር በሚገናኙበት ጊዜ ሁሉ የሚነጋገሩት



ነገርም አላቸው። የዛሬው ምሽት ንግግር ኪንዛን የሚመለከት ነው።

«ደስ የምትል ትንሽ ፍጡር ናት። ዓይነ ሥውር እንድትሆን መደረጉ ጭካኔ ይመስላል። ወደ ፊት ምን ልታደርጊያት አስበሻል ሮዝመሪ?» አለች ኤልሳቤጥ። በሦስት ዓመት ውስጥ ብሬይል እና የሳጠራ ሥራ ወደምትማርበትና ወደ አንድ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት እንድትሄድ እፈልጋለሁ:::: እንደዚያ ቢደረግላት፣ ለኑሮዋ የሚያስፈልጋትን ነገር ሠርታ ልታገኝ ትችላለች። ሥልጠናዋን ስትጨርስ ተመልሳ ወደ እኔ ትመጣለች፣» አለች ሮዝመሪ።

ጄኒ በፊቷ የነበረውን ብርጭቆ ለመድፋት ትንሽ እስኪቀራት ድ ረስ በጉጉት ወደ ፊት አሰገገችና፣ «የዓይነ ሥውሮች ትምህርት ቤ ት ነው አባዬ! ብላ ጮኸች።» የገና በዓል በደረሰ ጊዜ ሁሉ እሚጠሩን ቦታ። እማዬ ኪንዛ ወደዚያ ብትሄድ፣ አንዳንዴ እየመጣች ከእኛ ጋር ትቆያለች። እኔ ደግሞ እንከባከባታለሁ። ታናሽ እኅት እንዳገኘሁ ይሆንልኛል። እንደ ትልቅ ነገር አያታለሁ፣ እርሷም ከእኔ ጋር ስትሆን በጣም ደስ ይላታል። ትምህርት ቤቱ ውስጥ በጣም ደስ የሚል ጊዜ ነበራቸው። ኪንዛ ወደ ትምህርት ቤ ቱ የምትመጣው መቼ ነው አክስቴ ሮዝመሪ? አሁን ይዘናት ልንሄድ አንችልምን?» አለች።

እኅትማማቾቹ በጥያቄ ሁኔታ እርስ በርሳቸው ተያዩ።

«ጄኒ ያለችው መጥፎ አሳብ አይደለም። ትምህርት ቤቱ በጣም ጥሩ ነው። በጣም ትንንሽ ልጆችን ይቀበላል። ባለቤቴ የትምህርት ቤቱ የቦርድ አባል ስለሆነና ተሰሚነት ስላለው በቀላሉ እንድትገባ ሊያደርጋት ይችላል። ቶሎ ብትሄድ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ በፍጥነት ትማራለች። አንቺ ከምታመጪት ከእኛ ጋር በመኪና ልትሄድ ትችላለች፣» አለች የጄኒ እናት።

ሮዝመሪ አመነታች። የምትመልሰው ነገር ጠፋት። ሁሉ ነገር ድንገተኛ ሆነባት። ጄኒ በደስታ ወንበሯ ላይ ቁጭ ብድግ ትል ነበር።

«በረጅሙ የመኪና ጉዞ ጄኒ ይደክማታል። ሌላ ልጅ አብሯት

መኪናው ውስጥ ሲኖር ግን ሁልጊዜ በጣም ደስተኛ ትሆናለች፣» አለች የጂኒ እናት፡፡

«ምን እንደምል አላውቅም፡፡ አሳቡ በጣም ደግነታችሁን የሚገልጥ ነው. . . ነገር ግን ኪንዛ እርቃ ለመሄድ የማትችል ትንሽ ልጅ ትመስላለች፡፡ በነገሩ ላስብበትና ከአንድ ወይም ከሁለት ቀን በኋላ መልስ ልስጣችሁ?» አለች ሮዝመሪ፡፡

«ይቻላል፡፡ በፈለግሽ ጊዜ ንገሪን፡፡ ጂኒ ደግሞ ዝም ብለሽ ነገሩን አትደጋግሚው፡፡ ሰዎች በመጀመሪያ ትንሽ ሳያስቡ በጣም ጠቃሚ በሆነ ጉዳይ ላይ አይወስኑም፡፡ ሳያስቡ ከወሰኑ ይሳሳቱ ይሆናል፣» አለች የጂኒ እናት፡፡

«እኔ በጉዳዩ አስቤበታለሁ፣» አለች ጂኒ በሚያስደንቅ አነጋገር፡፡ ከዚያም ወደ አክስቷ ዘወር አለችና፣ «አክስቴ ሮዝመሪ፣ ኪንዛ ከእናንተ ጋር ትሂድ ብለሽ እንደምትፈቅጂ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ይህ አሳብ በሕይወቴ ካሰላሰልኳቸው ነገሮች ሁሉ የሚበልጥ ነው፡፡ እማዬና አባዬ እንኳን አሳቡ ጥሩ እንደ ሆነ ነው የሚያስቡት፡፡ አባዬ፣ አንተ የማትወደው አይስክሬም እዚያ አለልህ፡፡ እባክህ የምትወደው በማስመሰል ለመብላት ሞክር፡፡ ከዚያም እኔ ያንተንና የራሴን ድርሻ እበላለሁ፣» አለች፡፡

ጂኒ ሁለት አይስክሬሞች በማግኘቷ ደስታ ስለ ተሰማት፣ ለጊዜው የኪንዛን ጉዳይ ረሳችው፣ ሮዝመሪ ለመሄድ እስከ ተነሣች ድረስ ቤተሰቡ ስለ ሌላ ነገር ያወራ ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ የጂኒ እናት ሮዝመሪን እያየች፣ «እኔና ባለቤቴ አድርሰንሽ እንመለሳለን፡፡ ጂኒ ደግሞ ወደ መኝታሽ ሂጂ፣» አለች፡፡

«እሺ፣» አለች ሁለት አይስክሬሞች በማግኘቷ ደስ ያላት ጂኒ፡፡ ከዚያም የአክስቷን አንገት እቅፍ አደረገችና የሚነጋገሩትን ሌላ ሰው እንዳይሰማው ራሷን ወደ እርሷ ዝቅ በማድረግ አፏን ወደ ጆሮዋ አስጠግታ፡፡

«በነገሩ በጣም ልታስቢበት ነው አይደል፣ አክስቴ?» አለች፡፡

«አዎ፣ ጂኒ፣ በጣም አስብበታለሁ፡፡ ትክክለኛውን አቅጣጫ



እንዲያሳየኝም እግዚአብሔርን እጠይቀዋለሁ፡፡»

«እስከ ነገ ጠዋት ድረስ አቅጣጫውን ያሳየኛል ብለሽ ታስቢያለሽ?»

«አላውቅም፣ ጂኒ፣ ጉዳዩ ትልቅ ነው፡፡ ሁለት ቀን ስጪኝ!»

«በተቻለ መጠን ቶሎ እንዲፈቅድልሽ ጠይቂው፡፡ መልሱም እሺ የሚል እንዲሆን አሳስቢው፡፡»

«አንቺስ ልትጠይቂው አትችይም?»


«እንዴት እንደሚጠየቅ አላውቅበትም. . . ቢሆንም እሞክራለሁ፡፡ ደህና እደሪ፣ አክስቴ ሮዝመሪ፡፡»

«ደህና እደሪ፣ ጂኒ፡፡»

ሮዝመሪ አንገቷን ከሕፃኒቱ እጆች በቀስታ ካላቀቀች በኋላ፣ ከጂኒ እናትና አባት ጋር ጨለማ የሸፈነውን የገበያ ስፍራ እያቋረጡ ለመንገዝ ተነሡ፡፡ ሮዝመሪ ዘወር ብላ እጇን አወዛወዘች፡፡ ጂኒም በር ላይ እንደ ቆመች አጸፋውን መለሰችላት፡፡

## ምዕራፍ አሥራ አምስት

# ጄኒ አስቸጋሪ ትምህርት ተማረች



ሀሚድ የፀደዩን ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ተቀብሎታል:: የተበጣጠሰ አሮጌ ልብስ ደርቦ ክረምትን ማሳለፍ በጣም ይከብዳል:: እንግሊዛዊቱ ነርስ የሰጠችው ልብሶች ብጥስጥሳቸው ወጥቷል:: ቢሆንም፣ ይህ ከእንግዲህ ብዙ አያሳስብም:: አሁን የፀሐይ ብርሃን ስለሚያሞቅ ደስ ይላል:: አሞራዎች በከፍታ ስፍራ ጎጇቸውን ሠርተዋል:: አበቦች ተራራውን ሸፍነውታል:: ሸለቆው ውስጥ ያሉት የፍራፍሬ ዛፍ አበቦች ያምራሉ:: የፍየል ግልገሎች በየመንገዱ ላይ ይፈነጥዛሉ:: ሀሚድም፣ እንደ ሌሎቹ ልጆች፣ ትንሽ አድጓል፣ ነቃ ነቃም ብሏል:: በምቦሊኖ መሸጫው መደብር ደረጃ ላይ ተቀምጦ ዘይት የነካቸውን ጣቶቹን እየላሰ፣ ብሩህ በሆኑ ዓይኖቹ የገበያውን ግርግር በትኩረት ይመለከታል::

በገበያ ዕለት በጥድፊያ በሚመላለሱ ሰዎች መካከል ብዙ የሚታይ ነገር አለ:: ሀሚድ ኪንዛን ያያት ቁጭ ብሎ በሕዝቡ መሀል ሲመለከት ሳለ ነው:: ሀምራዊ ቀሚስ ለብሳለች:: ወደ ገበያ በወጣችው ነርስና በጄኒ መካከል ዘለል ዘለል ትላለች::



ወዲያው ሌላ ነገር ተመለከተ:: የሚያየው በህልሙ መሰለውና ዓይኖቹን አሻሽቶ እንደገና አፈጠጠ:: የሚያየው ሕልም አልነበረም:: ደነገጠ፣ ወደ ኋላ መለስ አለና መደብሩ ውስጥ ገብቶ ምድጃዎች መሀል ተደበቀ:: እዚያ ሆኖ፣ ጉድጓዷ ውስጥ በፍርሃት እንደ ተደበቀች ጥንቸል ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ ቀጥሎ የሚሆነውን ነገር ይመለከት ጀመር::

እንጀራ አባቱ ከመደብሩ ፊት ለፊት ቆሞ፣ ብርትኳን የሚገዙ ሰዎችን ትኩር ብሎ ይመለከታቸዋል:: ከዚያም አንድ ርምጃ ቀረብ በማለት ኪንዛን አያት:: አስተያየቱ የምትጫወት የጥንቸል ግልገልን ለመንደፍ የሚጠባበቅ እባብን ይመስላል:: የሕፃኗን ፊት፣ ነፃ ሁኔታዋንና ንግግሯን፣ ያደረገችውን ምቹ ጫማ እና ልብሶቿን በትኩረት ተመለከተ:: እነ ኪንዛ ወደ ዘይት ሻጩ ሲሄዱ ተከተላቸው:: ወደ እንጀራ ልጁ በጣም ቀርቧል:: ሀሚድ ይህን ሲመለከት እንጀራ አባቱ ኪንዛን ነጥቆ ይወስዳታል ብሎ ሰጋ:: አልነጠቃትም:: በገበያተኞቹ እየተከለለ በዝምታ ተከተላቸው:: ዓይኖቹ በቁጣ መቅላታቸውን እና ከንፈሮቹም ከብረት እንደ ተሠራ ወጥመድ ጥብቅ ብለው መግጠማቸውን ሀሚድ ተመለከተ::

ሀሚድ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ድንጋጤና ፍርሃቱ ለቀቀው:: የእንጀራ አባቱ የመጣው ለንግድ ስለሆነ ምናልባት በዚያው ምሽት ወደ መጣበት ይመለሳል:: ሀሚድን አላየውም፣ ምናልባትም ቶሎም አያየው ይሆናል:: ቶሎ ብሎ ወደ ተራራው በመሸሽ እስኪመሽለት ድረስ እዚያ ከሚኖሩት ዝንጀሮዎች ጋር ይቆያል:: ስለ ኪንዛ በፍጹም አልተጨነቀም:: በምትወዳት እና ፍጹም በማትለቅቃት እንግሊዛዊት ነርስ እጅ ገብታለች:: ቤቷ በእንጀራ አባቱ የማይጣስ ምሽግ ነው::

የሀሚድ አሠሪ በመጣ ጊዜ ረዳቱን መሆን በሚገባው ስፍራ ስላላገኘው ተገረመ፣ ተቆጣም:: ጆሮውን ቆነጠጠው:: ሀሚድ ምንም አልተሰማው፤ የዕለት ክፍያውን ከአሠሪው ተቀበለና ከመደብሩ ወጣ:: ከዚያም የእንጀራ አባቱ ከሚያደባበትና ለአደጋ ከሚያጋልጠው የገበያ ክልል በመሸሽ ወደ ከተማው ዳር ሄደ::

ኪንዛ፣ ጄኒ እና አክስት ሮዝመሪ የሚፈልጉትን ገዛዝተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ:: የተከተላቸውንና ቤታቸው ገብተው በሩን እስኪዘጉ ድረስ ይመለከታቸው የነበረውን ተንኮለኛ ሰውዬ አላዩትም:: የክሊኒኩ መከፈቻ ሰዓት ደርሷል:: አክስት ሮዝመሪ እዚያ በምትሠራበት ጊዜ፣ ኪንዛ ቤቱ ደረጃ ላይ ተቀምጣ ፀሐይ እየሞቀች ከድመቷ ጋር ትጫወታለች:: በሽተኞች ወደ ክሊኒኩ በሚመጡበት ጊዜ ወደ ውስጥ የሚገቡት እርሷን አልፈዋት ነው:: ይህ የቀድሞ ሁኔታ ነው:: ላለፉት ሁለት ሳምንታት ግን፣ ኪንዛ የምትጫወተው ከምትንከባከባትና ከምትወዳት ጄኒ ጋር ነው:: በዚሁ መሠረት ጄኒ ለአክስቷ ልታሳያት ያመጣችውን አዲስ የሕፃናት መጽሐፍ በአንድ እጇ፣ በሌላው እጇ ደግሞ ኪንዛን ይዛ እናትና አባቷ ወዳረፉበት ሆቴል በመሄድ ላይ ናቸው::

በጉዞ ላይ እያሉ አቅጣጫቸውን ለውጠው በገበያተኛው መሀል በማቋረጥ በሆቴሉና በእነርሱ መካከል ወደ አለው መናፈሻ ገቡ:: መናፈሻው ውስጥ ማንም አልነበረም:: ሰው ሁሉ ወደ ገበያ ሄዷል:: ፀጥ ያለው ሁኔታ ጄኒ ሽርሽር እንድትል ገፋፋት:: ስለ አዲሱ መጽሐፏ እያሰበች በመንሸራሸር ላይ እንዳለች ተቀምጣ ለማንበብ የሚያስችል አንድ ምቹ ቦታ ደረሰችና ለአምስት ደቂቃ ለማንበብ ወሰነች:: አክስቷ ቤት በምትሄድበት ጊዜ ሁሉ በመሀሉ የትም ቢሆን ጊዜ እንዳታሳልፍ እናቷ ነግራት ነበር:: አሁን ጄኒ ከአክስቷ ቤት መቼ እንደ ወጣች እናቷ አታውቅም:: በዚሁ መሠረት በአሮጌው መተላለፊያ አጠገብ አንድ ስፍራ መረጠችና ኪንዛን አጠገቧ በማድረግ እሚያምር ድንጋይ ላይ ተቀምጣ መጽሐፏን ታነብ ጀመር::

መጽሐፉ ውስጥ ያለው ታሪክ እንደ ጄኒ ስላለች ልጅ የተጻፈ ነው:: ልጅቱ የመሰናክል ዝላይ ውድድር የምታደርግበት ድንክዬ ፈረስ አላት:: ጄኒም ወደ ቤቷ በምትመለስበት ጊዜ በድንክዬ ፈረሷ የዝላይ ውድድር ለማድረግ ትፈልጋለች:: በትኩረት ታነብ ስለ ነበር፣ ኪንዛ ከአጠገቧ ተነሥታ ወደ መተላለፊያው መሄዷን እንኳን አላየችም ነበር:: ኪንዛ የሚገጫት ነገር መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ሁለት እጆቿን ወደ ፊት ዘርግታ ያለ መሪ ለመሄድ



ትችላለች:: በዚህ ሁኔታ ርቃ የሄደች መሆኑን ሲታወቃት ደግሞ ትቆምና ሰው መጥቶ ወደ ነበረችበት እንዲመልሳት ድምፅ ታሰማለች::

ጄኒ የመጽሐፏ ባለ ታሪክ የሆነችው አናቤል የምትጋልበው ፈረስ በሚጋደርገው የመሰናክል ዝላይ ውድድር አሸንፎ ዋንጫ መውሰድ አለመውሰዱን ለማወቅ እስከ ምዕራፉ መጨረሻ ለመድረስ በጉጉት ታነብባለች:: ይህን እያደረገች ኪንዛ መተላለፊያው አካባቢ መኖሯን በጨረፍታ ትመለከታት ነበር:: ተነሥታ ልታመጣት በማሰብ ላይ ናት:: ንባቧን ጨርሳ በደስታ ብድግ አለች:: አናቤል ውድድሩን በቀላሉ አሸነፈች:: ጄኒ በዚህ ደስ ቢላትም፣ ኪንዛን ብቻዋን እንድትሄድ ስለ ተወቻት ጥፋተኛነት ተሰማት:: «ኪንዛ!» ብላ እየተጣራች በአትክልቱ ስፍራ ወደ ሌላ አቅጣጫ ከሮጠች በኋላ ድንገት ቆመችና ዓይኖቿን በፍርሀት አፈጠጠች:: አካባቢው ባዶ ነው፣ ኪንዛ የለችም::

ልቧ በድንጋጤ እየዘለለባት ከቁጥቋጦ ቁጥቋጦ በመሮጥ፣ በደረጃዎቹ ላይ በመውጣትና በመውረድ እና እንደገና ወደ ነበረችበት በመመለስ ፈለገቻት:: ኪንዛ ጠፍታለች::

ጄኒ ድንጋጤ በከፊል ስለ አሳወራት ከመንገደኛው ሰው ጋር በመጋጨት፣ በመጋፋትና በመሹለክለክ እና በጭንቀት ዙሪያዋን እየተመለከተች ወደ ገበያው ስፍራ ሮጠች:: ጉንጮቿ በእንባ ርሰዋል፣ ዓይኖቿ በፍርሃት ፈጥጠዋል::

በመጨረሻ ትንፋሽ አጠራትና ቆመች:: ኪንዛን የምትፈልግበት ሌላ ስፍራ ስለሌለና፣ ትኩር ብለው የሚመለከቷትን ሰዎች ሁኔታ ስለ ጠላችው፣ ወደ መናፈሻው ተመለሰች:: መተላለፊያው ላይ ብቻዋን በመቆምም ምን ማድረግ እንደሚኖርባት ታስብ ጀመር::

ወደ ቤት ለመመለስ አልቻለችም:: አክስት ሮዝመሪ ኪንዛን በእምነት ሰጥታት ታማኝ ሳትሆን ቀርታለች:: ታዲያ አክስቷ ምን ትላለች? ከሁሉም የባሰው ነገር ኪንዛ ወዴት ሄደች? አንዳች አስከፊ ነገር ደርሶባት ይሆን? ፈርታ ወይም አንድ ጉዳት ደርሶባት ጄኒ ለምን አልደረሰችልኝም ብላ በማልቀስ ላይ ትሆን? ከዚህ ሁሉ

የቱ እንደ ደረሰባት ጁኒ ምንም አታውቅም:: እያለቀሰች እናትና አባቷ ወደ አሉበት ሆቴል ሮጠች:: ወደ ፎቅ በመውጣትም እናቷ እቅፍ ውስጥ ሽጉጥ አለች::

እናቷ የሆነውን ነገር ከጁኒ ከተረዳች በኋላ እርሷም በድንጋጤ ይበልጥ ነጣች:: የጁኒን እንባ ከጠራረገች በኋላ ያዘቻትና:-

«ወደ አክስት ሮዝመሪ ሄደን የሆነውን ነገር መንገር አለብን:: ወደዚያ ስንሄድ እግረ መንገዳችንን ገበያው ውስጥ ኪንዛን እንፈልጋታለን፣» አለች በቀስታ::

«ወደ አክስቴ ሮዝመሪ ለመሄድ አልችልም:: አልችልም እማዬ:: አንቺ ሂጂና ንገሪያት፣» አለች ጁኒ እንደ ቆመች:: አነጋገሯ ያሳዝናል::

«አይሆንም፣» አለች የጁኒ እናት በእርጋታ እና ጠንከር ባለ አነጋገር፣ «ራስሽ ሄደሽ መንገር አለብሽ:: አየሽ ጁኒ፣ ይህ የሆነው፣ አንቺ የማትታዘዢ እና የማትታመኚ ልጅ ስለሆንሽ ነው:: ስለዚህ ጠንካራ እና የሚገባሽን ወቀሳ ለመቀበል የተዘጋጀሽ መሆን አለብሽ:: አሁን በቶሎ ወደ ሮዝመሪ መሄድ አለብን:: ኪንዛ በሰው ተወስዳ ከሆነ፣ ጊዜ መባከን የለበትም:: አባትሽም ከእኛ ጋር ይሄዳል::»

ጁኒና ወላጆቿ ከሆቴል ሲወጡ ሁሉም ዝም ብለው ነው:: የጁኒ አባት አንድ አሳብ አቀረበ:: ሁለቱ ኪንዛን ለመፈለግ እንዲሄዱ እና እርሱ ደግሞ ወደ ገበያው ስፍራ በማምራት እንዲፈልጋት አሰበ:: ከአሥር ደቂቃ በኋላ ሦስቱም እንደገና ተገና ኙ:: አሁንም ዝምታና መጨነቅ ይታይባቸዋል::

«ቶሎ ወደ ሮዝመሪ ብንሄድ ይሻላል:: በቋንቋቸው እየተናገረች ሰዎችን ልትጠይቅ ትችላለች፣» አለ የጁኒ አባት::

በጉዞ ላይ እያሉ ሮዝመሪ ኪንዛን ለመፈለግ ወደ ሆቴሉ ስትመጣ አገኟት:: የሆነውን ነገር የጁኒ አባት ነገራት:: እርሱ በሚናገርበት ጊዜ፣ ጁኒ የአክስቷን ዓይኖች ለመመልከት ስላልደፈ ረች አልፍ ብላ መሬት መሬቱን እያየች ቆማ ነበር:: አክስቷ ምን



ትላለች? እገበያው መሀል ትቆጣት ይሆን? በዚያን ሰዓት ግን ስለ ግዴለሽነቷ ምንም የተባለ ነገር የለም:: ሁሉም የረሷት መሰሉ:: የሚያስቡት ስለ ኪንዛ ብቻ ነው::

በአንድ ላይ ሆነው በግንብ ወደ ታጠረው መናፈሻ ሄዱ:: እንዲያ ያደረጉት ሮዝመሪ ትክክለኛውን ስፍራ ተመልክታ በአቅራቢያው ያሉትን ባለ መደብሮች ስለ ኪንዛ ለመጠየቅ እንድትችል ነው:: ስለ ኪንዛ የሚነግራቸው ሰው ግን አላገኙም:: የሆነው ነገር ምንም ይሁን ምን የተፈጸመው በመተላለፊያው ሌላ አቅጣጫ ነው:: ያ ደግሞ ከመንገዱ እይታ በረጅም ግንብ ተ ከልሏል:: በዚያ በኩል ካለው የአትክልት ስፍራ የሚያስወጡ ሦስት በሮች አሉ:: አንደኛው የሚወስደው ጭር ወዳለው የገጠር መንገድ ሲሆን፣ ከጥቂት ኪሎ ሜትሮች ርቀት በኋላ ወደ አስቸጋሪ ተራራ ዎች ወደሚያመሩ ብዙ የእግር መንገድ ቅርንጫፎች ይከፋፈላል::

በአካባቢው የነበሩትን ሰዎች የመጠየቁ ነገር ምንም ጥቅም አለማስገኘቱ ከተረጋገጠ በኋላ ወይዘሮ ሮዝመሪ እንዲህ አለች:-

«እንግዲህ ሲሆኑ የሚችሉት ሁለት ነገሮች ናቸው:: አንደኛው ለለበሰችው ልብስ ሲሉ ሰዎች በድብቅ ወስደዋታል:: እንዲያ ከሆነ፣ ፖሊሶች ሊረዱን ይችላሉ:: ሁለተኛው የራሷ ዘመዶች እንደገና ስለ ፈለጓት ሰርቀዋታል:: እንዲያ ከሆነ፣ የተወሰደችው ለመልካም ነው:: ለነገሩ ለምን ወሰዳችኋት ብዬ ዘመዶቿን የመጠየቅ መብት የለኝም:: ከየት እንደ መጣች እንኳን አላውቅም:: የአካባቢው ልጅ የማውቀው አለመሆኗን ብቻ ነው ፣» ብላ አዲስ አሳብ የመጣላት ይመስል አሰብ አደረገችና፣ «ሀሚድ የት ይሆን ያለው? ከኪንዛ ጋር አንድ ዓይነት ቁርኝነት ያለው ስለ መሆኑ ሁልጊዜ አስባለሁ:: እርሱ አንድ ፍንጭ ሊሰጠን ይችል ይሆናል፣» አለች::

ነገር ግን የሚሆነውን ነገር ለማየት ከተሰበሰቡት ልጆች ሀሚድ የት መሆኑን የሚያውቅ አልነበረም:: በዚያን ጠዋት ሥራው ላይ ነበር፣ በኋላ ደግሞ በመጨረሻ የታየው፣ ወደ ተራራው ሲሄድ ነው:: ሁሉም ሲፈልጉት ፈቃደኞች ሆኑና በየአቅጣጫው ተ በታተኑ:: እንግሊዛዊቱ ነርስ ሀሚድን ለሚያገኘው ልጅ ጥሩ ነገር

እንደምትሸልመው እርግጠኞች ነበሩ:: ነገር ግን ሀሚድ ያለው ተራራው ላይ ስለሆነና በዝንጀሮዎች ላይ ድንጋይ በመወርወር ላይ በመሆኑ ማንም ሊያገኘው አልቻለም:: የእንጀራ አባቱ እንዳያገኘው ስለ ፈራ እና ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ ረጅም ጊዜ ስለ ቆየ፣ በልጆቹ ስብሰባ ላይ ሊገኝ አልቻለም:: እንዲህ ያለ ሁኔታ ከብዙ ሳምንት በኋላ የገጠመው ለመጀመሪያ ጊዜ ነው::

ፖሊሶቹ ስለ ጠፋችው ሕፃን የሰሙት በትሕትናና በኀዘኔታ ቢሆንም፣ ኪንዛ ትገኛለች የሚል ተስፋ ግን አልነበራቸውም:: ቢሆንም፣ በየተራራዎቹ ላይ ላሉት የመንግሥት የፍተሻ ጣቢያዎች ሁሉ ለመደወልና ዋና ዋናዎቹን መኪናዎችና ተጓዦችን እንዲፈትሹ ለማድረግ ቃል ገቡ:: ነገር ግን ሕፃኗ ብትገኝ እንኳን አብረዋት ያሉት ሰዎች ልጅ አለመሆኗን የሚያረጋግጥ ምን ማስረጃ አለ?

ሌላ ምንም ተስፋ ስላልተገኘ፣ ሁሉም ሻይ ለመጠጣት ወደ አክስት ሮዝመሪ ቤት ሄዱ:: ይሁን እንጂ፣ ማናቸውም የርሀብ ስሜት አልነበራቸውም:: ከትንሽ ቆይታ በኋላ የጂኒ እናትና አባት ወደ ሆቴላቸው ለመሄድ ተነሡ:: ጂኒም በድንጋጤ እንደ ገረጣችና ተስፋ እንደ ቆረጠች ተከተለቻቸው:: አሁንም ቢሆን ቀና ብላ አክስቷን ለማየት አልደፈረችም:: እርሷ ግን እንደ መጥፎ ልጅ አላየቻትም:: በጣም የሚያሳስባት ነገር፣ ኪንዛ ምን ገጥሟት ይሆን የሚለው ነው::

ሮዝመሪ ብቻዋን በመቅረቷ ደስ አላት:: ሻይ ማፍላቱንና ሌላውን ሥራ ካጠናቀቀች በኋላ ወደ ትንሽ ክፍሏ በመመለስ ስለ ኪንዛ ለመጸለይ ተንበረከከች:: ግልገሉ ድመት ትንሿን አጫዋች ልጅ፣ ጓደኛውን፣ ኪንዛን ማለት ነው፣ በመፈለግ አጠገቧ ይዘል ጀመር:: ኪንዛ የምትደገፈው ትራስ ሥር ከእንጨት የተሠራ አሻንጉሊቷ ተቀምጧል:: ሮዝመሪ የክፍሉን ውስጥ ስትመለከት የኪንዛን ኳስ፣ ምንጣፍ፣ ጂኒ የሰጠቻትን የጣፋጭ ምግብ መያዣ ሳጥን አየች:: ሮዝመሪ በምታየው ስፍራ ሁሉ፣ የጠፋችው ተወዳጅ ልጅ ምልክቶች ስለ ታዩዋት ራሷን እጆቿ ላይ በማንተራስ አለቀሰች:: ኪንዛ የት ሄደች? ምን ደርሶባት ይሆን? እንዴት ፈርታ



እና ቤቷን ናፍቃ ይሆን? ያለምንም ረዳት ባለማየት ጨለማ ውስጥ እንዴት ትሆን ይሆን? «አምላኬ ሆይ፣ ጠብቃት፣ ለጉዳት ወይም ለፍርሃት አታጋልጣት:: በደህና ወደ እኔ አምጣት፣» እያለች አለቀሰች::

በመጸለይ ላይ እያለች በጣም ዝቅ ያለ የለቅሶ ድምፅ ወይም ሳግ ከኋላዋ ሰማችና ክፍሉ ውስጥ ብቻዋን አለመሆኗን ተረዳች:: በፍጥነት ቀና ብላ ብትመለከት፣ ጂኒ በሩ ላይ ቆማለች:: ፊቷ እንደ ገረጣ ነው፣ ዓይኖቿ በለቅሶ አብጠዋል::

«ጂኒ ወዲህ መምጣትሽን እናትሽ አውቃለች?» አለች ሮዝመሪ በመደነቅ::

«አዎ፣ ለብቻሽ ላገኝሽ መፈለጌን ስለ ነገርኳት እስከ በሩ ያመጣችኝ እርሷ ናት:: በሩን ስላልቆለፍሽው ገባሁ:: ከእኔ ጋር ያለውን ጉዳይ ስትጨርሺ ወደ ቤት እንድትሸኚኝ ለምናሻለች:: ልታናግሪኝ ትፈልጊያለሽ ብዬ አላሰብኩም:: ምክንያቱም. . . ምክንያቱም የኪንዛ ነገር ሙሉ በሙሉ የእኔ ጥፋት ነው:: ምን ላድርግ አክስቴ?»

የመጨረሻ ቃላቷ በአዲስ እንባ የታጀቡ ነበሩ:: ሮዝመሪ ብድግ ብላ በመንቀጥቀጥ ላይ ያለችውን ሕፃን ወደ ቤት አስገባቻት፣ በሩን ዘጋችና አጠገቧ ተቀመጠች::

«ምንም ልታደርጊ አትችይም፣ ጂኒ:: እግዚአብሔር ግን እኛ ከምናደርገው ይበልጥ ጂኒን ስለሚወዳት፣ ማንኛውንም ነገር ሊያደርግ ይችላል:: እንንበርከክና ትንሿን ኪንዛን እንዲጠብቃት፣ እንዲያጽናናት እና በደህና እንዲያቆያት እንጸልይ፣» አለች በዝግታ::

በዚሁ መሠረት ተንበረከኩና ኢየሱስ ኪንዛን እንዲጠብቃት ሮዝመሪ ጸለየች:: ጂኒ ይበልጥ እያዘነችና እየተገረመች ጸሎቱን አዳመጠች:: አክስት ሮዝመሪ ደህና ናት ብላ አሰበች:: ሮዝመሪ አሳዛኝ ነገር በሚገጥማት ጊዜ፣ ይቅርታ፣ ሰላምና መጽናናት የምታገኝበት ስፍራ አላት:: ጂኒ ግን እንዲህ ያለውን መጠጊያ አታውቀውም:: ጨለማ ውስጥ የተዘጋባት መሰላት:: ኪንዛ

በእርግጥ ብትጠፋ፣ ጄኒ ለራሷ ይቅርታ እንደማታደርግና ሌላም ሰው ይቅርታ እንደማያደርግላት ተሰማት።

በሕይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ መጥፎ ፀባይዋ ያመጣው ነገርና ሁኔታው ያስከተለው አስከፊ ውጤት ለማምለጥ የማይቻል መሰላት። ሁልጊዜ የራሷን ፈቃድ ብቻ የምታደርግና የምትፈልገውን ካላገኘች በጣም የምትቆጣ ልጅ ነበረች። አባቷ እና እናቷ ግን ለእርሷ ደግ እና ይህን ፀባይዋን የሚረዱላት ናቸው። ለሦስት ወር ከታመመች በኋላም ይህንኑ ሁኔታዋን እንደገና አስታወሱት። አሁንም ሁልጊዜ እንደምታደርገው አልታዘዝ ብላ የመሰላትን ነገር አደረገች።

«ብቻ ኪንዛ በተገኘች። ሁለተኛ የማልታዘዝ እና መጥፎ ልጅ አልሆንም። ከዘላለም እስከ ዘላለም ጥሩ ልጅ እሆናለሁ፣» አለች ለራሷ።



# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

# የመታደግ ወይም የማዳን ዕቅድ



ሮዝመሪ የሚቀጥለውን ዕለት ያሳለፈችው ሀሚድን በማፈላለግ ነበር። እርሱ ግን ሆን ብሎ የተደበቀ ይመስላል። እንግሊዛዊቷ ነርስ ለምንድን ነው በተለይ ያን ጊዜ ባስቸኳይ የፈለገችው? ምናልባት የእንጀራ አባቱ ስላናገራት ብታገኘው ለእርሱ ልትሰጠው ይሆናል። ነገሩ አጠራጣሪ በመሆኑ ይሆናል ሀሚድ ከእርሷ ሊርቅ የወሰነው።

እንግሊዛዊቷ ነርስ ግን ልታገኘው ወስናለች። ሀሚድ ቀደም ብሎ ወደ ተራራዎቹ የሄደ መሆኑን ስለ ሰማች፣ የምትረዳቸው ልጆች ሊያደርጉት የነበረውን ስብሰባ በመሠረዝ ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት፣ እርሱ ከተራራዎቹ ይመለስበታል ብላ ወዳሰበችበትና ትልቅ ድንጋይ ወዳለበት መተላለፊያ ሄዳ ጠበቀችው። ብዙም ሳይቆዩ ነው ድንግዝግዝ ባለው ጨለማ ውስጥ ውልብ ሲል ያየችው። ፈጠን አለችና አሮጌ ሸሚዞቹን በመጨበጥ ያዘችው።

ሊያመልጥ በጣም ታግሏት ነበር፣ ፈጠን ብላ ድምጿን ስላሰማችው ግን ዝም አለና ቆመ። «ሀሚድ፣ ኪንዛ ጠፋችብኝ። በማፈላለግ ትረዳኛለህ? የምትሄድበትን ስፍራ ታውቀዋለህ?» አለች

በመማጠን አነጋገር።

ጥብቅ አድርጋ ስለ ያዘችው፣ ፊቷ እንደ ቆመ ግራ በተጋባ ሁኔታ ትኩር ብሎ ተመለከታት። በመጀመሪያ፣ አሳቡ በጣም ተበታተነበት። በኋላ ግን ቀስ በቀስ ተረጋጋ፣ አሳቡም ተሰበሰበለት። ኪንዛ ከጠፋች፣ ወደ ቤቱ የወሰዳት በእርግጥ የእንጀራ አባቷ ነው። ነርሷ ደግሞ የምትፈልጋት ስለ ኪንዛ እንጀራ አባት ምንም የምታውቀው ነገር የለም። ሀሚድ የሚያውቀውን ነገር ቢናገር ጥሩ ላይሆን ይችላል። ነገሩ ወደ ፖሊስ ይደርስ ይሆናል። ከፖሊስ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ለማድረግ የሚፈልግ የጎዳና ልጅ ደግሞ የለም። በሌላም በኩል፣ ወደ ቤተሰቦቹ እንዲመለስ የሚያደርገው ነገር ይፈጠር ይሆናል። ወይም የሚሰማው ነገር ሁሉ የማጥመጃ ተንኮል ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ማንኛውንም ነገር መካድና ከነገሩ መገላገል ይሻላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ኪንዛ ጠፍታለች፤ ካልተናገረ፣ ልፋቱ ሁሉ ከንቱ ይሆናል። ኪንዛ በጣም ደስተኛ፣ ጤነኛ እና በሰላም የምትኖር ነበረች። አሁን ግን ለለማኝ ትሸጣለች። የእንጀራ አባቷ ለዚህ ካልሆነ ለሌላ ለምን ይፈልጋታል? ሀሚድ ከዚህ ሁሉ ሊጠብቃት አልቻለም።

«ለነገሩ ምንም የማውቀው ነገር የለም፣» አለ ከብዙ ዝምታ በኋላ። እየጨነቀው ነው የተናገረው። ነርሷ ግን ብዙ ነገር የሚያውቅ ስለ መሆኑ በጣም እርግጠኛ ነበረች። የሚያውቀውን ነገር እንዲገልጥ ማድረጉ የሚያስቸግር መሆኑን ብታውቅም፣ ማግባባቷን በጥንቃቄ ቀጠለች።

«ወደ ቤት እንሂድና ራታችንን እንብላ። እዚያ እንነጋገራለን። ቀኑን ሙሉ ተራራው ላይ ስለ ዋልክ ርቦሀል፣» አለች ለስለስ ባለ አነጋገር።

ባለመሥራቱ፣ ካለፈው ምሽት ወዲህ የቀመሰው ምግብ ጥቂት ስለሆነ፣ በጣም ርቦታል። የርሀብ ቁርጠት ይሰማዋል። እንግሊዛዊቷ ነርስ ያቀረበችለትን ግብዣ ካልተቀበለ፣ በዚያ ምሽት ምግብ የሚያገኝበት ዕድል የለውም። የነርሷ ጥሪ ለሌላ ዘዴ



ስለሚሆን ወደ ቤቷ መሄዱ አደጋ ይኖረዋል ብሎም አሰበ። ነገር ግን በጣም ርቦታል!

ማንም እንድናገር ሊያደርገኝ አይችልም ብሎ አሰበ። ከዚያም ቆሻሻ እጁን ወደ ነርሷ ዘረጋው። እርሷም ጥብቅ አድርጋ ያዘችው። እቤቷ ደርሰው በርዋን ከኋላቸው እስኪዘጉ ድረስ አልለቀቀችውም።

ወደ ፎቅ አውጥታ ከዚያ ቀደም ኪንዛ ተኝታ ወደ አያት ክፍል ወሰደችው። ምድጃ ላይ ያለውን ትኩስ ሩዝና አትክልት ሽታ እያጣጣመ እግሩቹን አጣምሮ ምንጣፉ ላይ ተቀመጠ። ጎድጓዳ ሳህን ሙሉ ሩዝ እና ትልቅ ዳቦ ከሰጠችው በኋላ፣ ለራሷም አመጣች። በመብላት ላይ ሳለ፣ አሳቡ ሙሉ በሙሉ ምግቡ ላይ ስለ ነበረ፣ ምንም ጥያቄ አላቀረበችለትም። ነገር ግን ትኩር ብላ ትመለከተው ነበር። መልኩ ኪንዛን ነው የሚመስለው። ዓይኖቹ ጥቁርና ብሩህ ናቸው። ፊቱ የልብ ቅርጽ ያለው ሲሆን፣ አፉ ግጥም ያለ ነው። ምግቡን እስኪጨርስና የመጨረሻውን ጉርሻ እስኪጎርስ ጠብቃ እንደ ምንም ከተረጋጋች በኋላ፦

«ሀሚድ፣ ትንሿን እኅትህን ማን እንደ ወሰዳት ታውቃለህ? ካወቅህ ንገረኝ። ምክንያቱም እኔ ላመጣት እፈልጋለሁ፣» አለች ጠንከር ባለ አነጋገር።

በጣም ደክሟታል፣ ዝላለች። ግምቷ የተሳሳተ ይሆናል ብላም ፈርታለች። ንግግሯን ስትጨርስ፣ ጠንካራ የነበረው ንግግሯ ትንሽ ተንቀጠቀጠ። የድምጿ መንቀጥቀጥ ሀሚድን አበረታታው። የሮዝመሪ ንግግር ማታለል እንዳልሆነ ተረዳ። የአፍቃሪ ልብ እውነተኛ ጩኸት ነበር።

«እንጀራ አባቴ የወሰዳት ይመስለኛል። ትላንት ገበያ ውስጥ ሲመለከታት አይቼዋለሁ። አደባባዩ አካባቢ ሲከተላት አይቼው ነበር። ቢሆንም፣ ካንቺ ጋር ያለች ነበር የመሰለኝ፣» አለ።

ሮዝመሪ ጥረቷ  የተሳካ ስለ መሰላት ተደነቀች። ቢሆንም፣ ደስታዋን አልገለጠችም። በቀስታ እየተናገረች ቀጠለች ጥያቄዋን

«የት ነው እንጀራ አባትህ የሚኖረው?»

ሀሚድ የመንደሩን ስም ነገራት::

«ከእኔ ጋር እንደምትኖር አያውቅም ነበር?»

«አዎ፣ አያውቅም ነበር::»

ሌላ ነገር ገመተች ነርሷ::

«በዚያን ምሽት በሬ ላይ ያስቀመጥካት ለምንድን ነው?»

«እናቴ ናት እንደዚያ እንዳደርግ የነገረችኝ::»

«ለምን?»

«እንጀራ አባቴ ኪንዛን አይፈልጋትም:: ለአንድ ለማኝ ሊሸጣት ነበር:: እንዲያ ተደርጎ ቢሆን ኖሮ፣ ኪንዛ እንደ አሁኑ ደስተኛ አትሆንም ነበር:: ለዚህ ነው እናቴ ወደ አንቺ የላከቻት::»

«አሁንስ?»

«እንጀራ አባቴ ለለማኙ ይሸጣታል:: በሽያጭ የሚገኘውን ገንዘብ ይፈልገዋል::»

ይህን ስትሰማ ነርሷ ዘገነናት:: የኪንዛ የወደፊት ሁኔታ ከገመተችው በላይ እጅግ የከፋ ስለሚሆን፣ እንደ ምንም ልታድናት ይገባል:: አሁንም ቀስ እያለች ጥያቄዋን ቀጠለች::

«መንደሩ ምን ያህል ይርቃል?»

«በፈረስ ሁለት ቀን ያስኬዳል:: እንጀራ አባቴ የመጣው ግን ወደ ገበያ በሚመጣ ከባድ መኪና ሳይሆን አይቀርም:: በመኪና ከሆነ፣ ስድስት ሰዓት ብቻ ነው የሚያስኬደው»

«አንተስ እንዴት መጣህ?»

«አብዛኛውን መንገድ በእግር፣ የተወሰነውን በከባድ መኪና::»

«ኪንዛስ?»

«እኔ አዝያት»

በብርታቱና በድፍረቱ ነርሷ ተደነቀች:: ሀሚድ ለኪንዛ ሲል



ይህን ያህል ከደፈረ፣ አሁንም ይረዳታል! ብላ አሰበች::

«ወደ መንደራችሁ ብሄድና ለአባትህ ለማኙ ከሰጠው የሚበልጥ ገንዘብ ብሰጠው፣ ኪንዛን መልሼ እንድገዛት ይስማማል?»

«እኔ እንጃ፤ ይስማማ ይሆናል:: ብትሄጂ ቤቱን እንዴት ታውቂያለሽ? በተራራዎች የተከፋፈሉ ብዙ መንደሮች ናቸው ያሉት::»

«አብረኸኝ በመሄድ ታሳየኛለህን?»

«ለመሄድ አልችልም:: እንጀራ አባቴ በጣም ይደበድበኛል::»

«ቤቱ ድረስ መሄድ አያስፈልግህም:: በሩቁ ልታሳየኝ ትችላለህ::»

«የመንደሩ ሰዎች ሁሉ ስለሚያውቁኝ ለአባቴ ይነግሩታል::»

«በጂኒ ወላጆች መኪና እንሳፈርና በምሽት ጊዜ ወደ መንደሩ እንቀርባለን:: በምሽት ማንም አያይህም:: ይህን ሁሉ የምታደርገው ኪንዛን ለማዳን ነው::»

ሀሚድ ከፍርሃቱ ጋር እየታገለ በጥርጣሬ ራሱን አከከ::

«ሀሚድ፣» አለች በመማጠን አነጋገር:: «እምቢ ካልከኝ ላገኛት አልችልም:: ለማኙ ይወስዳትና ትልቅ ከተማ መንገድ ላይ ተቀምጣ ትሠቃያለች፣ ይበርዳታል፣ ይርባታል:: ዕድሜዋን ሙሉም በጨለማ ትኖራለች:: ወደ እኔ ብትመለስ፣ ደስተኛ ሆና ታድጋለች:: ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምራታለሁ:: እንዴት እንደምወዳትም ነግሬአታለሁ:: ስለ እርሱ ብዙ ጊዜ ነግሬሃለሁ፣ ሀሚድ:: ገና በእርሱ አላመንክምን?»

ሀፍረት ባለበት አስተያየት ቀና አለና ተመለከታት:: ዓይኖቹ ግን ብሩህ ናቸው:: «ጌታ ኢየሱስን በጣም እወደዋለሁ:: ጥፋቴን ሁሉ ይቅር ብሎኛል:: በልቤም ደስተኛ አድርጎኛል::»

«እንዲያ ከሆነ፣ ልብህን ጠንካራ ያደርገዋል:: ፍርሀትህን እንዲያስወግድልህና ኪንዛን እንዲያጽናናት አሁኑኑ እንጠይቀው፣» አለች በጥድፊያ::

ዓይኖቹን በእሺታ ከደነና ነርሷ በምትጸልይበት ጊዜ፣ እርሷ የተናገረቻቸውን ቃላት ደገማቸው:: በዚህ ሁኔታ በማሰላሰል ላይ እያለ ሁለት አሳቦች ወደ አእምሮው መጡ:: ጌታ ኢየሱስ በእርግጥ የሚወደው ከሆነ፣ እንጀራ አባቱ እንዲመታው አይፈቅድለትም፣ ስለዚህ፣ ምንም የሚያስፈራው ነገር አልነበረም:: ትልቅ፣ ፈጣን እና ግራጫ በሆነው የእንግሊዛዊው መኪና እስከ መንደሩ መጓዙ ደስ የሚያሰኝ መሆኑንም አሰበ::

በሚጸልይበት ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ በታወከው ልቡ ውስጥ ጠንካራ አሳቦችን አሳደረበት:: በመሆኑም፣ ጸሎታቸውን ባበቁበት ወቅት፣ በነርሷ አሳብ ለመስማማት በጣም ዝግጁ ነበር:: በመጨረሻ ከቤት የወጣውም ደስ እያለው ነው:: የገበያውን ስፍራ አቋርጦ በመሄድ ላይ እንዳለ በጉዞው ወቅት መኪናው መስኮት አጠገብ በመቀመጥ እንደ ንጉሥ በተኩራራ ሁኔታ ለጓደኞቹ እጁን ሲያወዛውዝ ታየው:: ወዲያው በደስታ ሳቀና ወደ ላይ ዘለለ:: እንጀራ አባቱ ገንዘብ ካገኘ ማንኛውንም ነገር ያደርጋል፣ ነርሷ ደግሞ ከለማኙ የበለጠ ገንዘብ ትሰጠዋለች::

እርሱ ከቤት እንደ ወጣ፣ ነርሷ ስለ ጉዞ ዕቅዷ ከጄኒ እናትና አባት ጋር ለመመካከር ወደ አረፉበት ሆቴል ሄደች:: ወላጆቿ ጄኒን ለሸርሸር ወደ ተራራው ይዘዋት ለመሄድ አስበው ነበር፤ እርሷ ግን ለመሄድ አልፈለገችም ነበር:: ቀኑን ሁሉ በጥሩ ስሜት ውስጥ አልነበረችም::

ያገኟቻቸው ማረፊያ ክፍላቸው ውስጥ አዝነውና ደክመው እንደ ተቀመጡ ነው:: ሁለቱም ሲያዩዋት ብድግ አሉና፣ «የሆነ ነገር አለ?» አሉ::

«አዎ፣» አለች ነርሷ:: ደስታዋን ለመደበቅ አልቻለችም:: ባዶው ወንበር ላይ ቁጭ ካለች በኋላ፣ ወደ ፊት ዘንበል ብላ እንዲህ በማለት አስደናቂውን ዜና ትነግራቸው ጀመር::

«በእርግጥ፣ ሳላማክራችሁ ነው ወደ ሀሚድ ሄጄ ነገሩን ያስተካከልኩት:: በአሰብኩት ዕቅድ ልትረዱኝ ፈቃደኞች እንደ ሆናችሁ እርግጠኛ ነኝ:: ምክንያቱም ስለ ኪንዛ በጣም የምትጨነቁ



ሰዎች ናችሁ:: ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ለመድረስ እንድንችል፣ ነገ ከሰዓት በኋላ ከዚህ መነሣት አለብን:: ስድስት ሰዓት ያህል የሚያስነዳ ጉዞ ነው:: እዚያ ደርሰን መኪናችንን ካቆምን በኋላ ስፍራው ለመድረስ ረጅም ርቀት መጓዝ የሚኖርብን መሆኑን ሀሚድ ነግሮኛል:: እኩለ ሌሊት ከማለፉ በፊት አንመለስም:: አንድ ጊዜ የምታደርጉት ስለ ሆነ ያስቸግራችኋል ብዬ አላስብም::»

«ኧረ በጭራሽ፣» አለች የጄኒ እናት ልክ እንደ ነርሷ ደስታ እየተሰማት:: በመቀጠልም፣ «ባለቤቴ ጆን አንቺን እና ሀሚድን ይዟችሁ ይሄዳል:: እኔ ከጄኒ ጋር እዚሁ እቆያለሁ:: ጄኒ መሄድ የሚያስፈልጋት አይመስለኝም፣» አለች::

«እዚህ እንድትቀር ቢደረግ ፍጻሜ የሌለው ችግር ይፈጠራል፣» አለ የጄኒ አባት:: ነርሷ እና የጄኒ እናት ይህን ሲሰሙ በደስታ የበራ ፊታቸው በተስፋ መቁረጥ እንደገና ጠቆረ::

«ጄኒ ተኝታለች እንዴ? የሆነውን ነገር ሁሉ ልነግራት እችላለሁ ወይስ እንቅልፍ ወስዷታል?» አለች ነርሷ ሮዝመሪ:: የጄኒ እናትና አባት ተያዩ እና ለትንሽ ጊዜ ዝምታ ሆነ:: ከዚያም የጄኒ እናት እንዲህ አለች::

«አዎ፣ ሂጂና ንገሪያት:: በተሻለና በተረጋጋ ሁኔታ እንድታነጋግሪያት እመኛለሁ:: በጣም ትወድሻለች፤ ዛሬ ማታ ደግሞ ከእርሷ ጋር የማደርገው ነገር ያለ አይመስለኝም:: ወደ ሽርሽር አልሄድም ስላለችን ደስታ የተለየው ቀን ነው ያሳለፍነው:: ከሽርሽሩ ይልቅ ኪንዛን በማፈላለጉ ረገድ አንቺን ለመርዳት ነው የፈለገችው:: እንደሚያማትና የጤና ችግር እንዳለባት አውቃለሁ:: ለዚህ ነው መሰለኝ፣ የምትፈልገውን ነገር ለማድረግ ካልቻለች ወይም አይሆንም ከተባለች ሞልቃቃና ነጭናጫ ትሆናለች::»

ለዚህ ነው ወደ ቤት እንደ ተመለስን ወደ መኝታዋ እንድትሄድ ያደረግኳት:: ቁጡነቷ ከፍ በማለት ላይ ነው:: ተቀጥታ ስለማታውቅ፣ ቅጣትን በጣም ትጠላዋለች:: አሁን በምን ሁኔታ ውስጥ እንደምታገኚያት አላውቅም:: ነገ እንድትሄድ ካልተፈቀደላት፣ በጣም ትበሳጫለች::»

«አይ ጄኒ! ልሂድና አላንቀላፋች እንደሆን ልይ፣» አለች ነርሷ ሮዝመሪ:: ከዚያም በቀስታ ወደ ፎቅ ወጣችና የጄኒን መኝታ ቤት በር አንኳኳች:: ከውስጥ ምንም መልስ አልተሰማም:: ትንሽ ጠበቀችና በሩን ከፍታ ወደ ውስጥ ገባች::

«ምን ትፈልጊያለሽ? አንቺ እንደ ነገርሽኝ ወዲያው አልተኛ ሁም:: እንደዚያ አድርጋለች ብለሽ እንዳታስቢ፣» አለች ጄኒ በአልጋው ልብስ እንደ ተሸፋፈነች በቁጣ::

«እኔ ነኝ ጄኒ፣» አለች ነርሷ በቀስታ ሄዳ አልጋው ላይ እየተ ቀመጠች::

ጄኒ ወዲያው የአልጋውን ልብስ አሽቀንጥራ በመጣል ፊቷን ገለጠች:: የድንጋጤ ስሜት ይታይባታል:: አክስቷ ነርስ ሮዝመሪ ፊት ሁልጊዜ በጨዋነት ነው የምትናገረው፣ ጥሩ ልጅ ናት ለመባል:: እናትና አባቷ ምናልባት ስለ እርሷ የተናገሩት ነገር ይኖራል:: ስለዚህ አመለካከቷን ለአክስት ሮዝመሪ ማስረዳት አለባት:: እንዲያ ቢሆን ብዙ በደል የደረሰባት መሆኗን ትረዳለች::

«አክስቴ ሮዝመሪ፣» አለች ጄኒ እያለቀሰች፣ «ስለ መጣሽ ደሽ ብሎኛል! ቀኑን ሙሉ ስለ ኪንዛ ሳስብ ነበር::

«በፍጹም አልነበረም፣ ጄኒ! ቀኑን ሙሉ ስለ ራስሽ ነበር ስታስቢ የዋልሽው፣ ለዚህም ነው ደስተኛ ያልሆንሽው:: ራሳቸውን የሚወዱ ሰዎች ሁልጊዜ ደስተኞች አይደሉም:: ምክንያቱም የሚፈልጉት ካልሆነላቸው በጣም ያስባሉ፣» አለች አክስት ሮዝመሪ እውነታን በሚገልጽ ድምጽ::

«ራስ ወዳድ አይደለሁም፣» አለች ጄኒ በቁጣ እያለቀሰች:: «እማዬና አባዬ የሚሉት እንጂ ሌላ ነገር አይገባሽም:: ኪንዛ ወዴት ሄዳ ይሆን እያልኩ ማሰቤን አላቆምም:: እማዬና አባዬ ግን ስለ ኪንዛ ምንም ወደማልሰማበት ስፍራ ወሰዱኝ::»

«አንዳች ነገር መስማትሽ ኪንዛን ምንም አይረዳትም:: ለመስማት ያለሽን ጉጉት ብቻ ነው የሚያረካው:: እናም ስላል ረካሽ፣ እናትና አባትሽ ቀኑን ሙሉ ደስ እንዳይላቸው አደረግሽ::



ይህ ራስ ወዳድነት ካልሆነ ምን ሊሆን እንደሚችል አላውቅም፣» አለች አክስት ሮዝመሪ::

ጄኒ ነርሷ ለተናገረችው ነገር የምትሰጠው መልስ ስላጣች እንዲሁ ብቻ፣ «አይገባሽም፣» አለች::

«አይደለም ጄኒ፣ በጣም ይገባኛል፣» አለች አክስት ሮዝመሪ፣ ከዚያም ፈጠን ብላ ጄኒ ፊት በመንበርከክ እና የተቆጣችውን ልጅ ወደ እርሷ ሳብ አድርጋ በማስጠጋት እንዲህ አለች፣ «ሁልጊዜ የምትፈልጊውን ነገር ሁሉ የምታገኚ መሆንሽን አውቃለሁ፣ እናትና አባትሽ የሚያስደስቱ እና ጥሩ ነገሮችን ስለሚሰጡሽ፣ ከራስሽ ደስታ ይልቅ በዓለም ውስጥ ስለ ምንም ግድ የለሽም:: ልብሽ አንቺን መካከል ያደረገ የተዘጋ ክብ ነገር ነው:: በመሆኑም፣ የሚጎዳ ወይም የሚያስቆጣ ነገር ሲመጣብሽ፣ የዓለም ፍጻሜ የደ ረሰ ይመስልሻል:: ጄኒ እያደግሽ በሄድሽ ቁጥር ከአሁኑ ይበልጥ የሚጎዱና የሚያስቆጡ ነገሮች ይገጥሙሻል:: በዚህ ሁኔታ ደስተኛ ያልሆነችና ፍቅር የሌላት ሰው ሆነሽ ልታድጊ ነው:: አየሽ በተ ገቢው ሁኔታ ሌላ ለመውደድ ጊዜ ወይም ስፍራ የለሽም:: ምክንያቱም ራስሽን በመውደድ ሥራ በዝቶብሻል::»

ጄኒ ጸጥ አለች:: ከዚህ ቀደም ማንም እንዲህ አልተናገራትም:: እናትና አባቷ ነገራቸውን የሚጨርሱት፣ «ግድየለም፣ ተይው ውዴ፤ አስበሽ ወይም ፈልገሽ አይደለም ያደረግሽው:: እንርሳው፤ ከእንግዲህ አናንሣው፣» በሚል ድምዳሜ ነው::

የአክስት ሮዝመሪ ንግግር ምናልባት ከፊል እውነት አለው:: ጄኒ ሁልጊዜ በጣም፣ በጣም ደስታ የራቃት ናት:: የዚህ ምክንያቱ ነገሮችን እንደ ፈለጋት ልታደርጋቸው አለመቻሏ ነው:: በትምህርት ቤት ስለ ነበረች አንዲት ልጅ አሰበች:: ልጅቷ ፈረስ መጋለብ ትፈልግ ነበር፣ በግብዣ ቀን አዲስ ልብስ መልበስ ትፈልግ ነበር::: ግን አንዱም አልሆነላትም:: ምክንያቱም አባቷ ይህን ሊያደርግላት የሚችል ሰው አልነበረም:: ልጅቱ ግን የፈለገችውን ባለማግኘቷ ችግር አልፈጠረችም:: በግብዣው ላይ የእኅቷን አሮጌ ቀሚስ ለብሳ ደስ ተሰኝታ እንደ ነበረች አሰበች:: ጄኒ እንዲህ ዐይነቱ ነገር

ሊገባት አልቻለም።

«ስለ ነገሮች ግድ የሌለኝ ሰው ልሆን አልችልም። ሰዎችን እወድዳለሁ፤ እማዬን፣ አባዬን፣ አንቺን ኪንዛንና ብዙ ሰዎችን።»

«ደስ ካሰኘንሽ ብቻ ነው የምትወጂን፣ የምትፈልጊውን ማድረግ ባቆምን ጊዜ፣ በእናትና በአባትሽ ላይ እንዳደረግሽው እኛንም ማበሳጨት ደስ ይልሻል።»

ጄኒ እንደገና ዝም አለች። አክስት ሮዝመሪ እንድትወዳት ለማድረግ መሞከሩ ጥቅም የለውም። ምክንያቱም ስለ እርሷ ሁሉንም የምታውቅ ትመስላለች። ቢሆንም፣ ንግግሯ ባልተለመደ ሁኔታ ደስተኛ አድርጓታል። በመሆኑም፣ ጄኒ የማስመሰል ድርጊቷን ወዲያውኑ ለማቆም የምትችል መሆኗ ተሰማትና እንዲህ አለች፦

ቀስ ብላ በመናገር፣ «ጥሩ እና ደስተኛ ለመሆን እፈልጋለሁ፣» አለች። «እማዬ ደስተኛ እንድትሆን ማድረግም እፈልጋለሁ። ነገር ግን አልችልም። ስለሚያስጨንቁኝና ላስወግዳቸው ስለማይቻለኝ ነገሮች በጣም የምጨነቅ እመስላለሁ።»

«አዎ፣ አውቃለሁ። ካለሽበት ሁኔታ የምትለወጪበት ብቸኛ መንገድ ኢየሱስን ወደ ልብሽ መጋበዝ ነው። ያን ጊዜ ወደ ሕይወትሽ ይመጣና እንድትለወጪ ይረዳሻል። በመጀመሪያ ግን የራስሽን እርምጃ መውሰድ አለብሽ። ኢየሱስን ይበልጥ በወደድሽው ቁጥር፣ ራስሽን ከሁሉ ይበልጥ መውደድሽን እየቀነስሽ ትሄጃለሽ። ኢየሱስ የሚፈልገውን ትፈልጊያለሽ፣ ቀስ በቀስ ደስተኛ እየሆንሽ ይበልጥ ትረኪያለሽ። ነገሩ የሚያስቸግር ቢመስልም፣ ግን በጣም ቀላል ነው፣» አለች አክስት ሮዝመሪ በዝግታ አነጋገር።

«ገባኝ፣» አለች ጄኒ በጣም ድክም ባለ አነጋገር። ማልቀሷን አቁማ በጸጥታ ተጋድማለች። አክስት ሮዝመሪ ለትንሽ ጊዜ ዝም ካለች በኋላ እንዲህ አለች፣ «የመጣሁት ስለ ኪንዛ አንድ ነገር ልነግርሽ ነው። የሄደችበትን አውቀናል። አባትሽ፣ ሀሚድና እኔ ወደ ቀድሞ ቤቷ እንሄዳለን። የምንሄደው እንጀራ አባቷ እርሷን እንዲሰጠን ልናግባባው ነው።»



«የት? መቼ? እንዴት?» አለች ጄኒ በመደነቅ ከአልጋዋ ላይ ነጥራ ቀና በማለት። ቀጠል አድርጋም፣ «ቶሎ በይና ነገሩን ሁሉ ግለጪልኝ! እኔም ለመሄድ እችላለሁ?»

«አይሆንም፣ ለመሄድ አትችይም። የምንመለሰው ዘግይተን ነው ብላለች እናትሽ። አምሽተን ነው የምንመጣው። ስለዚህ ምናልባት የምንሄደው ትንሽ ብንሆን ጥሩ ነው። ያለ ኩርፊያና ቁጣ ለመታዘዝ ዝግጁ ለመሆን ዛሬ ዕድል አለሽ። ኪንዛ የተወሰደችበትን ሁኔታ እና እንዴት እንደ ደረስኩበት አሁን እነግርሻለሁ፣» አለች አክስት ሮዝመሪ፣ ታሪኩን እየዘረዘረች ስትነግራት ኪንዛ ጋደም ብላ በጸጥታ አዳመጠች።

ሁሉም ነገር የሆነው በትክክል ነው፣ እርሷ ግን የሚገባት አልነበረችም። ትናንት ምሽት፣ «ኪንዛ ተመልሳ ከመጣች ለዘላለም ጥሩ ልጅ እሆናለሁ፣» በማለት ቃል ገብታ ነበር።

«አክስቴ፣ እማዬን ጥሪያት። ይቅርታ ልጠይቃት እፈልጋለሁ። ስለዚህ ነገ ጥሩ እሆናለሁ፣» አለች ጄኒ ፊቷን በከፊል ትራሱ ውስጥ ሸሽጋ በሹክሹክታ ነበር የተናገረችው።

# ምዕራፍ አሥራ ሰባት

## ደስ የሚል ምሽት



የሚቀጥለው ቀን ማለዳ ብሩኅና ጥርት ያለ ነበር። አስጥሎ የሚያመጣው ቡድን ጉዞ የጀመረው ከቀትር በኋላ ቀደም ብሎ ነው። ጄኒ እንድትሄድ ባለመደረጓ በጣም ብትናደድም፣ ተጓዦቹ በሚሄዱበት ጊዜ እጇን እያወዛወዘች ተሰናበተቻቸው። ሀሚድ በጣም በሚያምረው መኪና ውስጥ ለመሆን በመቻሉ ፍርሀቱን ሁሉ ረስቶ ኋላው ወንበር ላይ እንደ ልዑል ተኩራርቶ ተቀመጠና፣ በመገረም አፎቻቸውን ከፍተው ለሚመለከቱት እና በአድናቆት ከመኪናው ኋላ ለሚሮጡት የጕዳና ልጆች ራሱን ሽቅብ ቁልቁል በማድረግ ተሰናበታቸው። ቡትቶ ልብሳቸውን እየጎተቱና እየተንጫጩ ብዙ መንገድ ሸኙት። ሀሚድም እራሱን በመኪናው መስኮት ብቅ አድርጐ በድል አድራጊነት ድምፅ እየጮኸ ተሰናበታቸው። ሮዝመሪ ናት ሳብ አድርጋ ቁጭ እንዲል ያደረገችው።

ደስ የሚል ጉዞ ነበር። ሀሚድ ኪንዛን አዝሎ በዚያው አቧራማ ዳገት በሞቃት ቀን ያደረገውን አድካሚ ጉዞ አስታወሰ። ያኔ አካባቢውን ለማየት እስኪያቅተው ድረስ ስለ ደከመው ትዕይንቱን ለማድነቅ አልቻለም ነበር። አሁን ግን ሁሉንም ነገር ለማየት ፈለገ። በመሆኑም፣ ጎጆ ውስጥ እንዳለች ዝንጀሮ መኪናው ውስጥ ከወዲህ ወዲያ፣ ከወዲያ ወዲህ ይዘል ጀመር።



በኋላ ግን ኋለኛው መቀመጫ ላይ ጥቅልል አለና ተኛ። ከእንቅልፉ በሚነቃበት ጊዜ መኪናው በተራራዎች በተከበበ አንድ ስፍራ ቆሞ ነበር። የጄኒ አባትና ነርሷ ሳንዱዊችና ሻይ ይመገባሉ። ሀሚድም ክብ ኬክ ተሰጠው። ይህ ስለ ተደረገለት፣ መንግሥተ ሰማያት ውስጥ ያለ ያህል ተሰማው።

አሳቡን ያበላሸበት አንድ አሳብ ብቻ ነው። ፀሐይቱ ወደ ምዕራብ አድማስ እያሽቆለቆለች በሄደች መጠን፣ የሚጓዝበት መኪናም ወደ መንደሩና እንጀራ አባቱ ወዳለበት እየቀረበ ሄደ። የጄኒ አባትና ነርሷ ምንም እንደማይደርስበት ቃል ስለ ገቡለት፣ በጣም አልፈራም። ራሱን በእጆቹ ደግፎ ያሰላስል ጀመር። ወደ እናቱም እየተቃረበ ነው፣ በጣም አዘነላት። እርሷ ወዳለችበት ቀርቦ፣ ሊያያት ወይም ሊያናግራት አለመቻሉ በጣም ከባድ ነገር ነው። ሁለት ትልልቅ የእንባ ዘለላዎች ከዓይኖቹ ወጥተው መኪናው ወንበር ላይ ዱብ ዱብ አሉ።

ከትንሽ ጉዞ በኋላ መኪናው ከዋናው መንገድ ተገነጠለና ድንጋያማ በሆነው የተራራ መንገድ ይሽከረከር ጀመር። በቁጥቋጦ በተሸፈኑ ተራራዎች መካከል በቀስታ ተሽከረከረ። አካባቢው የተ ራራማው አገር ሰዎች የሚኖሩባቸው መንደሮች ያሉበት ነው። እ ረኞች ፍየሎቻቸውን ወደየቤታቸው በመውሰድ ላይ በመሆናቸው፣ እነርሱን ለማሳለፍ መኪናው አንዳንድ ጊዜ መቆም ነበረበት።

ፀሐይዋ ከተራራዎች ጀርባ ጠለቀች። ሀሚድ መንደሩ የሚገኝበትን ተራራ ቅርጽ በሩቁ ተመለከተ። ሁለት ብሩህ ከዋክብት ከበላዩ ያበራሉ። የልቡ ምት ፈጠነ፣ አፉ በጣም ደ ረቀበት።

የተለመደው ገበያ ስፍራ ሲደርሱ በጣም ጨልሞ ነበር። ጥቂት መደብሮች ያሉበትን አካባቢ አልፈው ኮረብታማው መንገድ አስቸጋሪ መሰናክል በሆነበት ቦታ ሲደርስ የጄኒ አባት መኪናውን አቆመ።

ነርሷ ከመኪናው ወርዳ አንድ ቤት በር ላይ የቆመን ልጅ መኪናውን እንዲጠብቅላቸው ስትጠይቀው፣ ሀሚድ እሮጦ ከአንድ

የወይራ ዛፍ ጀርባ ተደበቀ:: ነርሷ የምታነጋግረውን ልጅ ያውቀዋል፣ እርሱም ሆነ ሌላ ሰው እንዲያየው አልፈለገም:: ልጁ ዘወር እስኪል ድረስ ጠበቀና ከተደበቀበት ስፍራ አጎንብሶ ወጣና የጄኒን አባት እና ነርሷን ተከተላቸው:: ኪንዛን አዝሎ በሞቃቱ የበጋ ምሽት ከገበያ ወደ ቤት የሚጓዘው በዚህ ዳገትማ መንገድ ነበር:: ማለዳ ማለዳ እርሱና ራህማ ውኃ የሚቀዱበት ምንጭ የሚገኘውም እዚሁ ነው:: በስተግራው ያለው የመቃብር ስፍራ ነው:: ይህም አበቦች የሚበቅሉበት ስፍራ ሲሆን፣ ሦስት የልጆች መቃብሮች አሉበት:: ፊት ለፊቱ ያለው ተራራ አናት ላይ ባለችው መንደር ዳርቻ ካሉት ጎጆዎች የሚወጣው ብርሃን ይታያል:: ትንሽ እልፍ እንዳሉ የፋኖስ ብርሃን እና የከሰል ፍም የሚታይበትን የራሱን ጎጆ ተመለከተ:: ይሄኔ ቆም በማለት የጄኒ አባትና ነርሷ ወደ እርሱ እንዲጠጉ ጠቅሶ እንዲህ አላቸው:-

«ያውላችሁ፣ ከሾላው ዛፍ አልፎ ሦስተኛው ቤት ነው:: የግቢውን በር ገፋ አድርጉት፣ መቀርቀሪያ የለውም:: ውሻውን አትፍሩት፣ ታሥሯል፤ ለእንጀራ አባቴ ስለ እኔ ምንም እንደማትነግሩት ቃል መግባታችሁን አትርሱ::»

«አልረሳም ሀሚድ፣ ቃል ገብቼልሃለሁ:: ከእኛ ጋር መኪናው እስካለበት ድረስ የሚመጣ ከሆነ፣ እስኪመለስ ድረስ ተደበቅ:: ትተንህ አንሄድም:: እርሱ የማይመጣ ከሆነ፣ እዚሁ እናገኝሃለን፣» አለች ነርሷ በቀስታ::

የጄኒ አባትና ነርሷ እስከ ቋጥኛማው መተላለፊያ በቀስታ ሲጓዙ፣ ሀሚድ ደግሞ ከመቃብር ስፍራው በታች ያሉት ቁጥቋጠምች ውስጥ ለመደበቅ ሄደ:: ወደ መደበቂያው ስፍራ በቀስታ በመራመድ ላይ እንዳለ፣ በመጀመሪያ ከአካባቢው በጠፋበት ዕለት፣ በዕኩለ ሌሊት በተራራው ቁልቁል ሲወርድ በጉልበቱ ሲድህ የነበረበትን ሁኔታና ርኩሳን መናፍስትን የፈራበትን አጋጣሚ አስታወሰ:: ወዲያው ደግሞ ያን የመሰለው ፍርሀት እንደ ለቀቀውና ምክንያቱ ምን መሆኑን አስታወሰ:: ሞት ከእንግዲህ የጥላ እና የጠፉ መናፍስት መኖሪያ አይደለም:: ወደ እግዚአብሔር መኖሪያ ብርሃን እና የፀሐይ ድምቀት የሚያስገባ ነው:: ነርሷ



ደግሞ፣ የመልካምና የክፉ ነገር እውቀት የሌላቸው ትንንሽ ልጆች ወደዚያ እንደሚገቡ ነግራቸዋለች:: ስለዚህ የሞቱት ትንንሽ ወንድሞቹና እኅቶቹ ምናልባት እዚያ በመግባት ደስተኞች ሆነው ይሆናል:: እርሱም በገዛ መንደሩ እንደ ተጠላ ሰው ሲሸሽግ ከሚኖር ወደዚያ መሄድን ተመኘ:: እቤቱ ውስጥ የነበረውን ሞቃት የምድጃ ዳር፣ የሚያመነዥጉ ፍየሎች፣ ራኅማን እና ከሁሉም በላይ እናቱን ናፈቀ:: ልቡ ስለ እርሷ ተጨነቀ:: እዚያ መኖሩን ሰምታ ትመጣ ይሆን?

የጄኒ አባትና ነርሷ በባትሪ ብርሃን እየታገዙ ወደ ሀሚድ ቤት በሚወስደው ጭቃማ መንገድ ፊትና ኋላ ሆነው በመጓዝ ላይ ናቸው::

ማንም አላያቸውም:: አጥሩ በር ሲደርሱ ሀሚድ እንደ ነገራቸው ሆኖ አገኙት:: በሩ በትንሽ ግፊት ተከፈተ:: ወደ ውስጥ በመግባት ከጨለማው አለፉና፣ ክፍት ከሆነው የቤት በር በሚወጣው ኃይለኛ ብርሃን ውስጥ እያመነቱ ቆሙ::

ወዲያው የሰንሰለት ማቃጨል ተሰማና ትልቁ ጥቁር ውሻ ሲዘል ሰንሰለቱ ያዘው:: ቤቱ ውስጥ ተቀምጦ የነበረ ጢማም ሰው ወደ ውጭ ሲመለከት ስላያቸው፣ በፍጥነት ብድግ ብሎ ወደ ውጭ ወጣ:: ቤቱ ውስጥ የመደነጋገርና የጉርምርምታ ድምፅ ተሰማ:: ወዲያው የቤቱ ባለቤት ጠጋ ብሎ በፈገግታ፣ በትሕትና እና ጎንበስ በማለት ሰላምታ ሰጣቸው:: ወደ ቤት ውስጥ ገብተው የመጡበትን ጉዳይ እንዲነግሩትም ለመናቸው:: በቂ ባይሆንም እንኳን፣ ምግብ እንዲጋበዙም ጠየቃቸው:: በዚሁ መሠረት ጎንበስ ብለው በሩን በማለፍ ወደ ውስጥ ገብተው ደብዛዛ ብርሃን ባለው ክፍል ውስጥ በመቆም ውስጡን ተመለከቱ::

ኀዘን እና ትዕግሥተኛነት የሚታይባት ልጅ እግር ሴት እምድጃው ዳር ተቀምጣለች:: በጣም የምታፍር እና ጥቁር ዓይነ ውኃ ያላት ሕፃን ሴትዮዋ ሥር ሽጉጥ ብላለች:: ብዙም ብርሃን በሌለበት ጥግ እንደ መጋረጃ የተዘረጋ የብርድ ልብስ ላይ ደገፍ ያለች አሮጊት ሴት ተቀምጣለች:: ሰላምታ ልትሰጣቸው አልመጣችም፤

በጸጥታ እያየቻቸው በነበረችበት ጸናች:: የቤቱ ባለቤት ወለሉ ላይ ቁርበት በማንጠፍ ጀርባቸውን ወደ ሴትየዋ አድርገው እንዲቀመጡ ጠየቃቸው::

ኪንዛ በስፍራው የመኖሯ ምልክት የለም:: የነርሷ ልብ በፍርሃት ቀለጠ:: የደከሙት በከንቱ ሳይሆን አይቀርም::

ጢማሙ ሰውዬ እንዲያ በመሸ ጊዜ በመምጣታቸው መደነቁን በትሕትና ከገለጸ በኋላ፣ ልጅ እግሯ ሴት ሻይ እንድታፈላላቸው አዘዛት:: ሻዩ ቀርቦ እነ የጂኒ አባት ፉት በማለት ላይ እንዳሉ፣ ሰውየው የመጡበትን ምክንያት ጠየቃቸው::

«የመጣሁት ስለ ትንሿ ዐይነ ሥውር ልጅህ ሁኔታ ለመረዳት ነው:: ከሰባት ወራት በፊት በወንድሟ አማካይነት እቤቴ እንድትኖር ተደርጋ ነበር:: በጣም ስለ ወደድኳት እንደገና ልወስዳት በጣም እፈልጋለሁ:: ልጅህ ስለ ሆነች፣ የሚሆነው ነገር አንተ እንደ ፈለግክ መሆን አለበት:: እርሷን ለማግኘት ስል የሚጠየቀውን ዋጋ እከፍላለሁ:: እናቷም በየጊዜው እየመጣች ልታያት ትችላለች፣» አለች ነርሷ ጠንከር ባለ አነጋገር::

በክፍሉ ውስጥ ጸጥታ ሆነ:: ሲ መሐመድ በነርሷ ንግግር በተ ገለጸው ዋስትና እየተደነቀ አመነታ:: ገንዘብ ስለ መክፈል ጠቅሳለች:: እርሱ ደግሞ ለገንዘብ ሲል ማንኛውንም ነገር ያደርጋል:: ከለማኙ ይበልጥ ትከፍለዋለች:: በሌላ በኩል ደግሞ፣ ሰርቆ ስላመጣት ችግር ውስጥ ይገባ ይሆናል:: የሚያማምሩ ልብሶቿ ጥያቄም አለ:: ኪንዛ በቲማቲም ጆንያ ተጠቅልላ ከመሸ ነው ወደ ቤት የመጣችው:: ከዚያ ወዲህ ሰው እንዳያያት ተ ደርጋ ተሸሽጋለች:: ያን ዕለት ጠዋት ነው ልብሶቿን ለስፔይን ሰ ዎች የሸጠላቸው:: እንዲህ ባለው አስቸጋሪ ነገር ውስጥ መግባት ቀላል አይደለም:: የተገረመ ለመምሰል እየሞከረ መዳፎቹን ወደ ላይ በማድረግ እጆቹን ዘረጋና እንዲህ አለ፦

«የት እንዳለች እኔ አላውቅም:: እርግጥ ከሰባት ወራት በፊት ወንድሟ ሰርቋታል:: ከዚያ ወዲህ አላየኋትም፣ ስለ እርሷ የሰማሁት ነገርም የለም:: ቤቷ እዚህ መሆኑን የነገራችሁ ወንድሟ



ከሆነ፣ እውነት ነው የተናገረው:: ልጅቱ ግን እዚህ የለችም:: ካገኘ ኋት በደስታ ወደ አንቺ አመጣታለሁ፣» አለ በተሸነፈ ድምፅ::

በመካከላቸው ረጅም ዝምታ ሆነ:: የሮዝመሪ ዓይኖች፣ በምድጃው ሌላ አቅጣጫ ከተቀመጠችው ሴት ዓይኖች ጋር ተ ጋጠሙ:: የሴትየዋ ዓይኖች ትኩር ብለው ሮዝመሪን ይመለከታሉ፤ የምናብ ትእይንት ነው ወይስ ወደ እሮጊቷ በማመልከት በቀስታ ጠቀሰች?

ሮዝመሪ እተነጠፈላት ቁርበት ላይ እንደ ተቀመጠች እየተዟዟ ረች ክፍሉን በሙሉ በዓይኖቿ ቃኘች:: ኪንዛ ተደብቃበት ይሆናል ሊባል የሚችል አንድ ቦታ ብቻ ነበር ያለው:: ያም ከአሮጊቷ ጀርባ የተዘረጋው የብርድ ልብስ ነው:: ከእንግዲህ ስለ ትሕትና መጨነቅ አያስፈልግም:: ነርሷ በፍጥነት ብድግ አለችና ክፍሉን እያቋረጠች ድምጿን በጣም ከፍ አድርጋ ሦስት ጊዜ ኪንዛን በስሟ ጠራቻት::

ሰውዬው በድንጋጤ ብድግ አለና ቆመ:: አሮጊቷ ብርድ ልብሱን ጥብቅ አድርጋ ያዘች:: ድርጊቷ ግን የዘገየ ነበር:: በጣም የምታውቀውንና የምትወደውን ድምፅ የሰማችው ኪንዛ ለጥሪው ከፍ ባለ ድምፅ መልስ እየሰጠች ከብርድ ልብሱ ከለላ ውስጥ ለመውጣት ትታገል ጀመር:: ሮዝመሪ አሮጊቷን የመሸከም ያህል ገለል አድርጋት ስታልፍ፣ ኪንዛን ዳግመኛ በማትላቀቃት አኳኋን ጥብቅ አድርጋ አቀፈቻት::

የኪንዛ ደስታ ለመግለጥ ከሚቻል በላይ ሆነ:: ከሥቃይና ፍርሃትዋ ሁሉ ወጣች:: እንደገና በጠባቂዋ እጆች ገባች:: ያለፈው የሁለት ቀን ተኩል ጊዜ የቅዠት፣ የጭንቅና የብርድ ጊዜ ነበር:: በጆንያ እየተጠቀለለች አሮጌ መኪና ተሳቢ ላይ ነበር የምትተኛ ው:: ስታለቅስ እየተመታች፣ እየራባት፣ ግራ እየተጋባችና ከእናቷ እቅፍ መንጭቀው በወሰዷት ሸካራ እጆች ስትንገላታ ነው የቆየችው:: አሁን ግን ያ ሁሉ ሥቃይ አበቃ:: የተጨነቀው ሰውነቷ ዘና ብሎ ሰላም አገኘች:: ሮዝመሪ ዘወር ብላ የኪንዛን የእንጀራ አባት አየችው::

በሚያስፈራ ሁኔታ ቆሟል:: ፊቱ በቁጣና በፍርሀት ገርጥቷል::

የጀኒ አባትም ምናልባት ሰውዬው አንዳች ነገር ለማድረግ ቢሞክር ሊቋቋመው ተዘጋጅቶ ቆሟል:: ግዙፍ ሰው ነው:: ይህን የተ መለከተው ሲ መሐመድ አሁን ያለው ተስፋ፣ ቸርነትን ማሳየትና ጥሩ ድርድር ማድረግ መሆኑን ተገነዘበና፣

«አዎ፣ አገኘሻት:: ከእንግዲህ ያንቺ ልጅ ትሆናለች:: በጣም ትወድሻለች:: ከአንቺ ጋር ስትሆን ሰላም ያላትና ደስተኛ እንደምትሆን አውቃለሁ:: ንገሪኝ እስቲ እርሷን ለመውሰድ ምን ያህል ልትከፍይኝ ትፈቅጃለሽ?»

ሮዝመሪ፣ ለማኙ ይከፍለዋል ብሎ ሀሚድ ከነገራት ገንዘብ በጣም የሚበልጥ ዋጋ ጠቀሰችለት:: የኪንዛ ልብስ ጉዳይ ይነሣል ብሎ ስለ ፈራና ከእነዚህ ያልተጠበቁ እንግዶች ለመገላገል ሲል የተጠቀሰለትን ገንዘብ ለመቀበል ወዲያውኑ ተስማማ::

ኪንዛ እንዲህ ዋጋ የምታወጣ ወይም የተከበረች በመሆኗ የተ ሰማውን ደስታ በሚገልጥ ሁኔታ ፈገግ እያለ ገንዘቡን ሊቀበል ወደ ፊት ቀረበ:: አስፈሪው ድምፅ ወደ እርሷ መቅረቡን የሰማቸው ኪንዛ በፍርሃት አለቀሰች::

ሮዝመሪ ገንዘቡን ከሰጠችው በኋላ ወደ ፈራቸው ሕፃን ጎንበስ ብላ፣ «አይዞሽ፣ ኪንዛ አትፍሪ:: ከእንግዲህ አይነካሽም:: የእኔ ልጅ ሆነሻል፣» አለች በሹክሹክታ::

ኪንዛ ሁለት ጣቶቿን አፏ ውስጥ አድርጋ ዋስትናው በተ ረጋገጠ ስሜትና በእምነት በጸጥታ ተኛች:: እርካታና ፍርሃት በራቀው ስሜት ወዳጇ እቅፍ ውስጥ ዘና ብላ አረፈች:: እንቅልፍ የወሰዳት ወዲያው ነበር:: ለእርሷ ሲባል ረጅም ጉዞ እንደ ተደ ረገና፣ ወደ ነበረችበት እንደገና ለመመለስ ከፍተኛ ዋጋ እንደ ተ ረገና ከፈለላትም አላወቀችም:: ውሸት ነግሯት የማያውቀው ድምፅ ግን፣ «አትፍሪ፣ የእኔ ልጅ ሆነሻል፣» ብሏታል::

ሌላ ችግር ከመፈጠሩ በፊት በተቻለ ፍጥነት ከመሄድ በቀር የቀ ረ ነገር አልነበረም:: ሮዝመሪ አሮጊቷን እና የኪንዛን እንጀራ አባት በአጭሩ ተሰናበተቻቸውና የኪንዛን እናት ለማናገር ዘወር አለች:: ከሰሉ ምድጃ አጠገብ ያለው መቀመጫዋ ግን ባዶ ነበር:: ዓይናማዋ



ትንሽ ልጅ ብቻ ነበረች ቀጭ ብላ ፍዝዝ ባለ አኳኋን የምትመለከተ ው:: የገንዘቡ ክፍያ በሚፈጸምበት ጊዜ ነው የኪንዛ እናት ማንም ሳያያት ሹልክ ብላ የወጣችው:: የባልዋ ቁጣ ምንም ሳይመስላት፣ ድምጿን በጣም ዝቅ አድርጋ ልጇን ሀሚድን እየጠራች በጠባቡ መንገድ ቁልቁል በመገስገስ ላይ ናት::

ያለ እርሱ ምሪት ቤቱን ሊያገኙት እንደማይችሉ ስላወቀች፣ በአቅራቢያው እንደሚኖር ገምታለች:: ያም ሆኖ አንድ ትንሽ ልጅ በመቃብሩ ስፍራ ዳር ካሉት የወይራ ዛፎች ጥላ ሥር ወጥቶ እጇን በሳመው ጊዜ ግር ብሏት ነበር:: ፍርሀት በተሞላበት ሁኔታ ወደ ዛፎቹ ጥላ ውስጥ መልሳ ከጎተተችው በኋላ ትኩር ብላ እያየችው፣ «ትንሹ ልጄ፣ ትንሹ ልጄ እንደ ምን አለህልኝ? ደህና ነህ?» አለች በሹክሹክታ::

«በጣም ደህና ነኝ:: ከተማው ውስጥ ሥራ በመሥራት ላይ ነኝ:: የኪንዛ ነገር እንዴት ነው፣ አገኟት?» አለ እርሱም በሹክሹክታ::

«እንግሊዛዊቷ ሴት ገንዘብ ከፍላ ልጇ በማድረግ ልትወስዳት ነው:: ከእንግዲህ ስለ ኪንዛ ምንም አልፈራም:: ማንኛውም ነገር መልካም ይሆንላታል:: ከእንግዲህ አትሠቃይም፣ አትደበደብም፣ ወይም አትለምንም:: አንተ ግን፣ . . . ውዱ ልጄ ወደ እኔ ና፣ በጣም ትናፍቀኛለህ::»

«እንዳልሽው ለማለት አልደፍርም:: ሲ መሐመድ እየደበደበ ይገድለኛል:: ሠርቼ ለመኖር እችላለሁ:: እንግሊዛዊቷ ነርስ ራታችንን ታበላናለች:: በተጨማሪም ልጆችን ያቅፋል ብላ ስለ ነገ ረችኝ ኢየሱስ የተጻፈ መጽሐፍም አለ:: መጽሐፉ ውስጥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ስለሚያደርሰው እግዚአብሔር ተጽፏል:: ከመጽሐፏ የምትነግረን ነገር ልቤን ደስ ስለሚያሰኘው ይበልጥ ለማወቅ እፈልጋለሁ፣» አለ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለበት::

ንግግሩ ቅንነት የሞላበት ስለ ነበር እቅፍ አደረገችው:: ቁመቱ ቢረዝምም፣ ሰውነቱ ቀጭን ነው:: አሁንም በጣም ትንሽ ልጅ መስሎ ታያት:: ቢሆንም፣ በራሱ ጥረት ደስታን አግኝቷል::

በሚናገርበት ጊዜ በጨረቃ ብርሃን ፊቱ ብሩህ ሆኖ ይታያት ነበር:: ምን ነው ተከትላው በሄደች:: አሁን ባለችበት ቦታና ሁኔታ ደስታ የላትም::

«ወደ ቤት መመለስ አለብህ ልጄ:: እኔም ደስተኛ ለመሆን እፈልጋለሁ:: የእንጀራ አባትህ አይደበድብህም:: ፍየሎችን የሚጠብቅለት ልጅ መቅጠር አለበት:: እዚህ ሆነህ ሳታገለግለው በመቅረትህ ሁልጊዜ ያጉረመርማል:: ወደ ቤት ብትመለስለት ደስተ ኛ ይሆናል፣» እያለች ገፋፋችው::

ራሱን ትከሻዋ ላይ አስደግፎ በጸጥታ በመቀመጥ ያሰላስል ጀመር:: በጉዞ፣ በመንከራተት፣ ራሱን በመጠበቅና በዕድሜው ራሱን የቻለ ሰው ለመሆን በመጣር ደክሞታል:: የሚፈልገው ነገር እንደገና ትንሽ ልጅ መሆን ነው፣ ለጥቂት ጊዜ ያለ ፍርሃት በጨለማው ውስጥ እናቱ ላይ ደገፍ ብሎ ማረፍና ወደ ቤቱ መሄድ::

እንደዚያ ቢያደርግ ግን፣ ከነርሷ መጽሐፍ ማንበብን የመማር ዕ ድል እንደገና አይገጥመውም:: ምናልባትም ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚወስደውን መንገድ ይረሳዋል:: እንጀራ አባቱን አሁንም ይፈራዋል:: ከረጅም ጸጥታ በኋላ ቀስ እያለ ውሳኔ አደረገ፣ በሹክሹክታ እንዲህ አለ፣ «አሁን ወደ ነርሷ ቤት እመለስና ወደ መንግሥተ ሰማያት ስለሚወስደው መንገድ ከሚናገረው መጽሐፍ እማራለሁ:: ከዚያ በኋላ ምርት የመሰብሰቢያው ጊዜ ሲደርስ እመጣና ስለ ተማርኩት ነገር እነግርሻለሁ:: ሲ መሐመድ እንዳይደበድበኝ ብቻ ንገሪው::»

የሰዎች እርምጃ ተሰማና የባትሪ ብርሃን ወደ እነርሱ በራ:: ወዲያው ብድግ አሉና ወደ ጨረቃው ብርሃን ወጡ:: የሀሚድ እናት ከልጇ ከመለየቷ በፊት ፈጠን ብላ ሳመችው:: ከዚያም ነርሷን ከመረቀቻት በኋላ የልጇን እጅ አስያዘቻት:: ከዚህ በኋላ ምንም ሳትናገር መለስ ብላ በዳገታማው መንገድ ወደሚጠብቃት ቅጣት አመራች:: ቢሆንም፣ እርካታና ድፍረት ይታይባት ነበር:: ኪንዛ ለዘላለም ዋስትና አግኝታለች፣ ትንሹን ልጇን ሀሚድንም



አይታዋለች:: ሁሉ ነገር መልካም ሆኖላታል፣ እንደገና እንደሚመጣም ቃል ገብቷል:: ምንም የሚያሳስባት ነገር አልነበ ረም::


እነሀሚድ በፍጥነት ወደ ሸለቆው ሄዱ:: የጂኒ አባት ኪንዛን ሲሸከማት ነርሷ ባትሪውን ይዛለች:: መንገዱን በጥሩ ሁኔታ የሚያውቀው ሀሚድ ከፊት ቀድሞ ይመራቸዋል:: መኪናው እቆመበት ስፍራ ሊደርሱ ሲሉ ከኋላቸው ፈጣን እርምጃና የቁጣ ድምጽ ሰሙ:: ሲ መሐመድ ነበር የጠፋ ልጁን፣ ሀሚድን ለመፈለግ የመጣው:: የሚስቱ ከቤት ውስጥ መሰወር ነበር ጥርጣሬ ያሳደረበት:: ወደ ቤት በምትመለስበት ጊዜ ፊቷ ላይ የታየው ደስታ ደግሞ ጥርጣሬውን አረጋገጠለት::

«እንጀራ አባቴ!» አለ ሀሚድ ከአዳኝ እንደምትሸሽ ጥንቸል ወደ መኪናው እየሮጠ:: በሮቹን ለመክፈት ሲሞክር የተቆለፉ ስለ ሆኑበት በፍርሀት ድምጽ እየለፈለፈ ይዘል ጀመር:: ነርሷ በቅርብ ትከተለው ነበር:: የጂኒ አባት ኪንዛን እንደ ተጠቀለለ ጨርቅ ወርወር አድርጎ አስታቀፏት፣ የመኪናውን በር ከፍቶ በፍጥነት በመግባት የመኪናውን ሞተር አስነሣና የኋላ በሮቹን ከፈታቸው:: ነርሷ፣ ኪንዛና ሀሚድ በድል አድራጊነት በሚያንጎራው መኪና ውስጥ እየተጣደፉ ገቡ:: በጣም በሚያስፈራ ሁኔታ እየዘለለ ባዶውን የገበያ ስፍራ አቋርጦ ተሽከረከረ:: ሲ መሐመድ ባሕር ዛፍ ሥር በጣም እንደ ተናደደ ብቻውን ቆሞ ቀረ:: እንጀራ ልጁ ሀሚድ በሚያንጸባርቁ ትራሶች ላይ በመደገፍ ይስቅ ጀመር::

ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ ተረጋጉ፣ ተመቻቹ፣ ፍርሀቱም ለቀቃቸው:: ኪንዛ፣ ባለፉት ሦስት ቀናት በደረሰባት ሽብር እና ስጋት የተነሣ ደክሟት ስለ ነበር፣ ሰላማዊ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰዳት:: ሀሚድ እጆቹን የመኪናው መስኮት ላይ አሳርፎ ከቤቱ በላይ ያሉትን መንታ የተራራ ጫፎች እያየ ይደነቃል:: በአንድ የበጋ ምሽት፣ ሰብሉ በሚጎመራበት ጊዜ ብቻውን በእግሩ ተ መልሶ እንደሚመጣ ያውቃል:: (ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 8:12 ላይ ኢየሱስ፣ «የሚከተለኝም የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ ከቶ በጨለማ አይመላለስም፣» ብሎ ስለተናገረ አይፈራም::

*ምዕራፍ አሥራ ስምንት*

# አዲስ ጅማሬዎች



አባቷ፣ ሮዝመሪ እና ሀሚድ ኪንዛን ለመታደግ (ከወሰዳት ሰውዬ ለማስለቀቅ) በሄዱ ጊዜ ጄኒ በሆቴል ውስጥ ያሳለፈችው ረጅምና አሰልቺ ቀን ነበር:: ለማሰብ ብዙ ጊዜ ያገኘችበት ቀን ነበር::

ስለ ኢየሱስ ይበልጥ ለማወቅና፣ መጽሐፍ ቅዱስ ኖሯት ስለ እርሱ ለማንበብ ተመኘች:: ክሊኒኩ ውስጥ ስላለው ሥዕል አሰበችና፣ ኢየሱስ ልጆችን እንደሚወድ፣ እንዲሁም ወደ ልቧ ገብቶ ሊለውጣት መፈለጉን አረጋገጠላት:: ነጭናጫ፣ ሞልቃቃ እና ከንቱ ከመሆን ጠንካራ፣ ደስተኛ እና ሰው የምትወድ ልትሆን ትችል ነበር:: «ብርሃኑ ያበራ ዘንድ ባዶ ፋኖስ ውስጥ የተለኮሰ ሻማ እንደ ማኖር ነው፣» በማለት ተናግራ ነበር አክስት ሮዝመሪ::

ጄኒ «ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ እባክህ ወደ ሕይወቴ ና፣» አለችና ጸለየች::

በዚያን ምሽት ለመተኛት እስከማትችል ድረስ ስለዚሁ የምታስበው ብዙ ነገር ነበራት:: ቢሆንም፣ ዓይኖቿን ጨፈነቻቸው:: ከዚያ በኋላ ያወቀችው ነገር እናቷ በቀስታ ነቅነቅ ያደረገቻት መሆኗን ነው:: አክስት ሮዝመሪ ኪንዛን በጨርቅ ጠቅልላ



እንዳቀፈች ጄኒ አልጋ አጠገብ በመቀመጥ ትስቃለች::

«ኪንዛ ናት!» አለች ጄኒ ኪንዛን እያቀፈችና እየሳመቻት:: ገና እኩለ ሌሊት ስለ ነበር፣ የሆቴሉን ሌሎች እንግዶች እንቅልፍ ላለመንሳት በሹክሹክታ መነጋገር ነበረባቸው:: ኪንዛን ለማምጣት ስለ ተደረገው ነገር ሁሉ ጄኒ ለማወቅ ፈለገች::

ከጉዞ የተመለሱት ሁሉ ርቧቸው ስለ ነበር ቁርስ ተዘጋጀ:: የጄኒ እናት ቅቤና ማር የተቀባ ዳቦ ፣ እንዲሁም ብስኩት አቀረበችላቸው:: እንደዛ ደስታ የተሞላበት የእኩለ ሌሊት ግብዣ ተደርጎ አያውቅም:: ጄኒ ያን ሰዓት ስታስታውሰው እንደምትኖር ተገነዘበች:: ኪንዛ ተመልሳ መጥታለች:: የጄኒ መጥፎ የልጅነት ጥፋት ይቅርታ ተደርጎለታል፣ ተረስቷል:: አዲስ ልጅ ሆና በአዲስ ደስተኛ ሕይወት ልትኖር ነው:: በሰዎች ተከብባ አልጋዋ ላይ እንደ ተቀመጠች የቀረበውን ምግብ በአፏ እየሞላች ትመገብ ጀመር:: በዙሪያዋ ያሉትን ሰዎች ወደደቻቸው:: ደስታዋ እጅግ የበዛ ሆነ:: እናቷ በተዳከመ ድምፅ ሁሉም መተኛት ያለባቸው መሆኑን በመደጋገም ብታሳስብም፣ የሰማት አልነበረም:: ሁሉም በሹክሹክታ ማውራታቸውንና መመገባቸውን ቀጠሉ:: የጄኒ አባት ኪንዛን ይዘው ከሲ መሐመድ ያመለጡበትን ሁኔታ በሚነግራቸው ጊዜ በደስታ ወደ ኋላው ወደቀ:: ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ላለመሳቅ ሁሉም ተጠነቀቁ:: ኪንዛ ከእንቅልፏ ነቅታ ቁጭ በማለት እንደ ጉጉት ጫጩት ዓይኖቿን ዝግት ክፍት ታደርግባቸው ጀመር:: ይህን የእኩለ ሌሊት ፍንደቃ የወደደችው አትመስልም:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ በተጠቀለለችበት ጨርቅ ላይ ጋደም በማለት እንደገና አንቀላፋች:: የጄኒ እናት ለአምስተኛ ጊዜ ሁሉም ወደየመኝታቸው እንዲሄዱ በማሳሰቧ ባለቤቷ፣ «እውነት ነው፣ መተኛት አለብን:: መጀመሪያ ግን አንድ የዳቦ ቁራሽ ልብላ:: ከአልጋ ላይ መውደቅ እንደገና አስርቦኛል፣» አለ:: አክስት ሮዝመሪ፣ ጄኒ እና እናቷም እንዲሁ ለመመገብ ፈለጉ::

የጄኒ እናት ትንሽ ቆይታ መተኛት ያለባቸው መሆኑን ለስድስተኛ ጊዜ አሳሰበች:: ይሄኔ ሁሉም ታዘዟት:: ሁሉም ጄኒን፣ «ደኅና እደሪ» በማለት እየሳሙ እና ትከሻዋን መታ መታ እያደረጉ

ከክፍሉ ወጡ:: ከዚያም በጄኒ አባት አወዳደቅ እየተሳሳቁ በፎቁ ደረጃዎች ወደ ታች ወረዱ:: እርሱ ግን በትልቅ ጫማው በጥፍሩ እንደሚራመድ ዝሆን እየሄደ ዝም ብሎ ነበር:: ጄኒ ከደስታዋ ጋር ብቻዋን ቀረች:: እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቷል:: ኪንዛ ተመልሳ መጥታለች::

በማግሥቱ ሰው ሁሉ እስከ ረፋዱ አንቀላፋ፣ ከሀሚድ እና አክስት ሮዝመሪ በቀር:: ሁለቱ ከእንቅልፋቸው የነቁት በተለመደው ሰዓት ነው:: ሀሚድ የጄኒ አባት ይነዳው በነበረ መኪና ውስጥ ደህና አንቀላፍቷል:: ሮዝመሪ ቀድማ የተነሣችው ግን ብዙ ሥራ ስለ ነበራት ነው:: አንድ ሰው የመኝታ ቤቷን በር ባንኳኳ ጊዜ ገና ማለዳ ነበር:: በድካም መነፈስ ተነሣች:: በሯን በምትከፍትበት ጊዜ ያገኘችው ሀሚድን ነበር:: በምንጩ ውኃ ስለ ታጠበ ፊቱና እጆቹ ያበራሉ::

የለበሰው ጨርቅ በጣም ተቀዳዷል፣ ቆሽሿልም:: እግሩ ላይም ከባድ ቁስል አለበት:: ቢሆንም ደስተኛ፣ የተነቃቃና ፊቱ እንደ ጸደይ ጠዋት የሚያበራ ልጅ ሆኗል:: የነርሷን እጅ ሳመና እየሳቀ በሩ ላይ ዘለለ:: ለአንድ የተለየ ምክንያት የመጣ ይመስላል:: ምን ማለት እንዳለበት ግን አላወቀም:: «ኪንዛ እንዴት ናት?» አለና ጠየቀ::

«በጣም ደህና ናት:: ገብተህ ልታያት ትፈልጋለህ?» አለች ነርሷ::

ለነርሷ ጥያቄ መልስ ያደረገው ነገር፣ ኪንዛ ወደ ተኛችበት ክፍል ለመሄድ ከፊት ቀድሞ በፎቁ ደረጃዎች ሽቅብ መሮጥ ነው:: ኪንዛ አንድ ጥግ እጇን ተንተርሳ ምንጣፍ ላይ በመተኛት ታንቀላፋለች:: ሀሚድ ደስ ብሎት ራሱን አወዛወዘ:: ከዚያም የሚበላ ነገር ይኖር ይሆናል በሚል ተስፋ የክፍሉን ውስጥ ተመለከተ:: እንግሊዛዊቷ ነርስ ቁርሷን በመመገብ ላይ ስለ ነበረች የመጣው በትክክለኛው ጊዜ ነበር:: እግሮቹን አጣምሮ ብሩህና ተስፋ የሚታይባቸውን ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ ወለሉ ላይ ተቀመጠ:: ባለፈው ሌሊት እንደ ሌሎቹ በማር የተዘጋጀ ሳንድዊች



ስላልበላ በጣም ርቦታል::

ነርሷ በጎድጓዳ ዕቃ ከቡና የተሠራ የሚጠጣ ጣፋጭ ነገርና ትልቅ ዳቦ ሰጠችው:: በአፉ ሙሉ ዳቦውን እየጎረሰ፣ ከሚጠጣው ነገር ፉት ይል ጀመር:: መመገቡን አብቅቶ ያዘቀጠ ስኳር እንዳይኖር የጎድጓዳውን መጠጫ ውስጥ በጣቱ እየጧጠጠ ወደ ነርሷ ጠጋ አለና፣ «ንባብ አስተምሪኝ፣» አለ::

ነርሷ በጥርጣሬ ትኩር ብላ እያየችው፣ «ብዙ ሰዎች ንባብ ለመማር ይፈልጉና ለአሥራ አምስት ቀን ብቻ ነው ትምህርቱን የሚከታተሉት:: ከዚያ በኋላ ያቋርጣሉ:: በዚህ ሁኔታ ጊዜዬ በከንቱ ይባክናል፣» አለች::

«ምርት የሚሰበሰብበት ጊዜ እስኪደርስ በየቀኑ እማራለሁ፣» አለ በቁርጠኛነት አነጋገር:: «ያኔ ወደ አገሬ እሄዳለሁ:: እንጀራ አባቴ በምርት መሰብሰብያ ጊዜ በጣም ሥራ ስለሚበዛበት ሲያየኝ ደስ ይለዋል:: ከዚያ በፊት ንባብ ለመማር እችላለሁን?»

«በየቀኑ ከመጣህ የምትችል ይመስለኛል፣» አለች ነርሷ:: ሥራ የሚበዛበት መሆኑን እያሰበች መቼ ልታስተምረው እንደምትችል አሰላሰለች:: ልጁ ንባብ ለመማር የጓጓና የወሰነ ይመስላል::

«ለምንድን ነው ንባብ ለመማር የምትፈልገው ሀሚድ?» አለችና ጠየቀችው::

ቀና ብሎ እያያት ቀላልና ትንሽ ታሪኩን እንዲህ እያለ ነገራት:- «ወደ መንደሬ ለመሄድ እፈልጋለሁ:: ወደዚያ ከሄድኩና ለማንበብ የማልችል ከሆንኩ፣ መንግሥተ ሰማይ ስለሚወስደው መንገድ ማን በቀጣይነት ያስተምረኛል?»

«ኢየሱስ ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚወስድ እውነተኛ መንገድ መሆኑን ታምናለህ ማለት ነው?»

«አዎ፤ አንድ ሕልም አይቻለሁ:: ጌታ ኢየሱስ እጆቹን ዘርግቶ አየሁት:: በመስቀል ላይ ያለ ይመስለኛል:: ከመስቀሉ ጀርባ በሰፊው የተከፈተ አንድ በር ነበር:: በሩ ወደ እግዚአብሔር የሚወስድ መንገድ መሆኑን ነገረኝ:: ከዚያም ወደ አንቺ

እንድመጣ ነገረኝ:: ምክንያቱም ማንኛውም ነገር አንቺ ዘንድ ያለው መጽሐፍ ውስጥ ተጽፏል::»

«ጥሩ ነው:: ሁልጊዜ በዚህ ሰዓት ልትመጣ ትችላለህ:: አሁኑኑ እንጀምራለን፤» አለች::

ከዚያም በአረብኛ ፊደል የተጻፈ መጽሐፏን ፈልጋ ታስተምረው ጀመር:: ፈጣን ተማሪ ሆኖም አገኘችው:: በግማሽ ሰዓት ውስጥ ብዙ ፊደሎችን ተማረ:: በጉብዝናውም ደስ አለው::

«አአ-ዲ-ዲዲ-ርር--ዚ፤» ሲል ቆየና «አሁን ለማንበብ እችላለሁ!» አለ ድምጹን ከፍ አድርጎ::

በኩራት ቀና ብሎ እየዘለለ ወጣ:: ነርሷም ደስ እያላት ቁርስ የተበላበትን ዕቃ ለማነሣሣት ሄደች::



# ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ
# የአክስት ሮዝመሪ ገለጻ



አሁን የበዓሉ ጊዜ ሊያልቅ ነው:: በመጨረሻው ቅዳሜ ማለዳ ሁሉም የሚያስፈልጋቸውን ቁሳቁስ ይዘው ለሽርሽር ወደ ተራራ ዎች ወጥተዋል::

የሣር ጎጆዎች ያሉባቸውን መንደሮች እያለፉ ሽቅብ ወደ ተ ራራው ነዱ:: ከዚያም የእንግሊዝ አበቦች በዙሪያቸው ወደ በቀሉባቸው ትልልቅ የጥድ ዛፎች ጥላ ታጠፉ::

ጄኒ እና አክስት ሮዝመሪ ቢጫ አበባዎችን መልቀም ጀመሩ:: በዚህ ጊዜ ጄኒ አዲሱን ምሥጢሯን ለአክስቷ ለመንገር ፈለገች:: ሌላ ዕድል ሊኖራት ስለማይችል ዛሬውኑ ልትነግራት ይገባል:: ነገር ግን ታሪኩን እንዴት በማለት መጀመር እንዳለበት አላወቀችም:: ለአክስቷ መንገር የምትችልበት ትክክለኛ ዕድል እንዲገጥማት ጸለየች:: በጣም ጠቃሚ ነገር እንደ ሆነላት እርግጠኛ ነበረች:: ከዚህ በኋላ ምን መጠበቅ እንደሚኖርባት አክስት ሮዝመሪ እንድትነግራት ፈለገች:: ቀኑ አለፈ፤ ትክክለኛ የመጠየቂያ ጊዜ ያገ ኘች አትመስልም::

ሲመሽ በመኪናቸው ወደ ቤት ተመለሱ:: ጄኒ ራሷን አባቷ

ትከሻ ላይ አስደገፋለች:: ለአክስቷ ለመግለጥ የፈለገችውን ነገር ለመናገር ባለመቻሏ ተበሳጭታለች:: አንዳንድ ጥርጣሬዎችም ወደ አሳቧ ይመጡ ጀመር:: ዝቅተኛና ወንዝ በሚያቋርጠው ሜዳ ላይ በመንዝ ላይ ናቸው:: በወንዙ ዳር አበቦች በቅለዋል:: የሚቀጥለው ዕለት የፋሲካ እሑድ መሆኑን ጀኒ አስታወሰችና በፍጥነት ቀና ብላ ተቀመጠች::

የፋሲካን እሑድ በጣም ትወድደዋለች:: በዚያን ዕለት ሁልጊዜ በመመገቢያው ጠረጴዛ ላይ ነጫጭ አበቦች ይደረጋሉ:: በመመገቢያ ሳህኗ ዙሪያ ደግሞ በቀለም የተኸጎረጎሩ ትላልቅ እንቁላሎች ይቀመጣሉ:: ከቁርስ በኋላ በተለያዩ አበባዎች ወደ አማረው ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ:: ነጫጭ ልብስ የለበሱ ልጆች፣ «ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬ ተነሥቷል፣ ሃሌሉያ!» እያሉ ይዘምራሉ::

ይህ ሁሉ እዚህ የለም:: ምክንያቱም የሚኬድበት ቤተ ክርስቲያን የለም:: ጀኒ ግን ነጫጭ አበባዎችን ይዛ አክስት ሮዝመሪን ልትጎበኛት ወሰነች:: ምናልባት ያን ጊዜ ምሥጢሯን ልትነግራት ትችል ይሆናል:: እጇን አባቷ እጅ ላይ አሳረፈችና፣

«አባዬ፣ አቁም፣» አለች::

እርሱም መኪናውን አቆመና፣ «ምን ሆነሻል?» በማለት ጠየቃት::

«አንድ ነገር እፈልጋለሁ፣» አለች:: ከዚያም ከመኪናው ዘልላ ወረደችና የምታደርገውን ነገር እንዳያዩባት ወደ ኋላ ትንሽ ሮጠች:: ሜዳው ላይ እየተሯሯጠች ከውኃው ዳር በእጇ ሙሉ አበቦች ለቀመችና በሹራቧ ጠቅልላ ወደ መኪናው ተመልሳ ሮጠች::

«ምንድን ነው የያዝሽው፣ ጀኒ?» አለና ጠየቃት አባቷ::

«ምሥጢር ነው፣ አሁን ጉዟችንን ልንቀጥል እንችላለን!» የትንሿ ልጇን ድርጊት በኋላው መስኮት በኩል ትመለከት የነበ ረችው የጀኒ እናት ሳቀችና ዝም አለች:: ጀኒ አልጋዋ ውስጥ እስክትገባና አበባዎቹ ውኃ ባለበት ዕቃ ውስጥ መዘፍዘፋቸውን እስክታይ ድረስ የሚሆነው ነገር ሁሉ ምን መሆኑን አልተረዳችም



ነበር::

«እማዬ፣ ነገ የፋሲካ እሑድ ነው:: በፋሲካ ዕለት ሁልጊዜ ነጫጭ አበቦች ይኖራሉ:: በጠዋት ተነሥቼ አበቦቼን ለፋሲካ በዓል እንኳን አደረሰሽ በማለት ለአክስቴ ልወስድላት እችላለሁ?»

«እንዴት፣ እንዴት ደስ የሚል አሳብ ነው:: አክስትሽ በጣም ትወድሻለች ጀኒ:: ስትነቂ ልትሄጂ ትችያለሽ:: እዚያው በመቆየት አብረሻት ቁርስ ትበያለሽ ብዬ አስባለሁ:: የምትለብሽውን ንጹሕ ልብሶች አሁን አወጣልሻለሁ::»

እንዳለችውም የጀኒን ምርጥ ልብሶችና ንጹሕ ካልሲዎች ካወጣችላት በኋላ በደህና እደሪ ብላ ስማት ወጣች:: ጀኒም የማለዳውን መምጣት እየናፈቀች ወዲያውኑ እንቅልፍ ወሰዳት:: ሁሉም ነገር በትክክል እየተከናወነ ነው::

ከእንቅልፏ የነቃችው እንግሊዝ ውስጥ ያሉት አብያተ ክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት የተነሣ መሆኑን ለሕዝብ ለማስታወስ የደውል ድምፅ በሚያሰሙት ማለዳ ነው:: ዘልላ ከአልጋዋ ወረደች:: የፋሲካ ዕለት በመሆኑ ተጣጥባ በጣም በጥንቃቄ ለበሰችና ከቤት ወጣች::

በሩን ስታንኳኳ፣ ቁርሷን በመመገብ ላይ የነበረችው አክስት ሮዝመሪ፣ እንዲያ ባለው ማለዳ እንግዳ በመምጣቱ እየተገረመች፣ በመስኮት ብቅ አለች:: የመጣው ማን መሆኑን ካየች በኋላ በሩን ለመክፈት ከፎቁ ቁልቁል ተንደረደረች:: ጀኒ በደስታ ገባችና አበባውን ወደ አክስቷ እየዘረጋች:-

«ነጫጭ አበቦች ለፋሲካ!» አለች በደስታ ድምፅ:: «አንቺ ሳታይኝ ነው ትላንት የቀጠፍኳቸው፣» አለች በድል አድራጊነት ስሜት::

ቁርስ ወደ ተዘጋጀበት ወደ ላይኛው ክፍል አብረው ሄዱ:: ቁርሱ የተዘጋጀው ነጭ ልብስ በለበሰ ጠረጴዛ ላይ ነው:: መሐሉ ላይ የሚበላውና የሚጠጣው ነገር ተቀምጧል:: ጀኒ ያመጣችውን አበባ በጥሩ የአበባ ማስቀመጫ አድርገው ጠረጴዛው ላይ

አስቀመጡትና ቁጭ ብለው ቁርሳቸውን ይመገቡ ጀመር::

«በፋሲካ ዕለት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ዝግጅትን ይመስላል፣ አይመስልም አክስቴ? በአገራችን በፋሲካ ዕለት እማዬ፣ አባዬና እኔ ሁልጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሄዳለን:: እዚህ ቤተ ክርስቲያን አለመኖሩ ያሳዝናል፣ አያሳዝንም? ቢኖር ኖሮ ሁላችንም እንሄድ ነበር፣» አለች ጄኒ::

«አዎ፣ ቤተ ክርስቲያን የመሄድ ዕድል የለም:: ቢሆንም፣ ጄኒ በአንድ በኩል ሲታይ፣ ብዙም የሚያሳስብ ነገር አይደለም:: ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚኬድበት ዋና ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ነው:: እግዚአብሔርን የትም ልናገኘው እንችላለን:: በየዕለቱ ክፍሌ ውስጥ አገኘዋለሁ:: አሁን አንቺ በምትመጪበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የፋሲካን ታሪክ ሳነብ ነበር::»

«መመገብሽን ካበቃሽ ታሪኩን ልታነቢልኝ ትችያለሽ?» አለች ጄኒ፣ አክስት ሮዝመሪ ታሪኩን ስታነብላት ለማዳመጥ ተመቻችታ እየተቀመጠች::

«ኢየሱስ ማርያምን አትክልት ውስጥ አገኛት:: ከደቀ መዛሙርቱ አንዳንዶቹን ትንሽ ክፍል ውስጥ አገኛቸው፣ ሌሎቹን ሁለቱን በመንገድ ላይ፣ ጴጥሮስን ደግሞ ባሕር ዳርቻ ላይ አገኛ ቸው፣ አየሽ እንግዲህ፣ ሕንፃ ወዳለበት ስፍራ መሄድ የግድ አስፈላጊ አይደለም::»

«አዎ፣ አያስፈልግም:: ይህንኑ ነው ልነግርሽ የፈለግኩት:: ያኔ . . . ኪንዛን ለመፈለግ በሄዳችሁበት ዕለት እላይ ተራራው ጫፍ ላይ እርሱ እኔን ያገኘኝ ይመስለኛል:: ልክ ፋኖሱ ውስጥ እንዳለው ብርሃን ኢየሱስ እውስጤ እንዲኖር፣ እንዲሁም ራስ ወዳድና ብስጩ እንዳልሆን እንዲያደርገኝ ጠየቅኩት:: ወዲያውኑ ደስታ ተሰማኝ፣ እንደ ጠየቅኩት ወደ ውስጤ የገባም መሰለኝ:: ትናንትና ግን የሆነው ነገር ሁሉ እውነት ነው ወይ እያልኩ አስብ ጀመር:: አክስቴ እውነት ኢየሱስ ወደ እኔ መጥቷል? ይህን የምልበት ምክንያት የተለየሁ ሰው መሆኔ ስለማይሰማኝ ነው::»

አክስት ሮዝመሪ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብላ ቆየችና፣ «ማርያም



እንዴት ነው ኢየሱስ በእርግጥ ወደ እርሷ የመጣ ለመሆኑ እርግጠኛ የሆነችው?» አለች በቀስታ::

«ስሟን በጠራው ጊዜ ነው:: እርግጠኛ መሆን ለእርሷ በጣም ቀላል ነበር:: ድምጹን ሰምታለች፣ አይታዋለችም::»

«አዎ፣ ይህን አውቃለሁ:: እግዚአብሔር እውነት ተናጋሪ መሆኑን ብናምን፣ እርግጠኛ መሆኑ ለእኛም ቀላል ነው:: አንድ ነገር ላንብብልሽ፣ ጄኒ:: ከዚያ በኋላ አንድ ታሪክ እነግርሻለሁ::»

«በጣም ጥሩ፣» አለች ጄኒ:: ታሪኮችን መስማት ትወዳለች:: አክስት ሮዝመሪ የምታነበውን መጽሐፍ ቅዱስ ለማየት ተጠጋችና ሁለቱም ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 43 ቁጥር 1ን አነበቡት:-

*«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ ተቤዥቼሀለሁና አትፍራ፣ በስምህ ጠርቼሃለሁ፤ አንተ የእኔ ነህ?»*

«ይህ ጥቅስ ልንፈልጋት በሄድንበት ምሽት ኪንዛ የነበረችበትን ሁኔታ ያስታውሰኛል፣» አለች አክስት ሮዝመሪ፣ ኪንዛ ወደ ተኛ ችበት ስፍራ እየተመለከተች:: «ቀደም ሲል ከእኔ ጋር በደስታ ትኖር ነበር፣ ግን ተሠረቀችና ከእኔ ተወሰደች:: ኪንዛን በጣም እወዳታለሁ፣ በሄደችበት ስፍራ ደስተኛ እንደማትሆንም አውቃለሁ:: ስለዚህም ፈለግኳት፣ በፍርሀትና በርሀብ ላይ ሆና አገኘ ኋት:: ትጠብቀኝ ነበር:: እዚያ መኖሬን አላወቀችም፣ እኔ ግን እዚያ እንዳለች አውቅ ነበር:: ስለዚህም ምን አደረግኩ?»

«ድምጽሽን ከፍ አድርገሽ በስሟ ጠራሻት!» አለች ጄኒ ዓይኖቿ እያበሩ:: ታሪኩን በደንብ ብታውቀውም፣ ደጋግማ ብትሰማው አይሰለቻትም::

አክስት ሮዝመሪ ሳቀችና፣ «እውነት ነው፣ በስሟ ጠራኋት:: ኪንዛ አልኩ:: ታዲያ ኪንዛ ምን አደረገች?»

«ወዲያውኑ በተደበቀችበት ጩርቅ ውስጥ ሆና ተፈራገጠች!» አለች ጄኒ::

«ደስተኛ አልነበረችም፣ ፈርታ ነበር:: ወደ እኔ ብትመጣ

ደህንነቷ የተጠበቀና ደስተኛ እንደምትሆን ታውቃለች:: ስለዚህ በቀጥታ ወደ እቅፌ በመምጣት ፍጹም ዋስትና ያላት ሆነች:: ታምነኝ ነበር:: እና ተራራው ላይ አንቺ የገጠመሽ ሁኔታ ይህ ነው ጄኒ:: ስለ ኢየሱስ ብዙ አታውቂም ነበር:: ጎስቋላና ራስሽን የጠላሽ ሰው ነበርሽ:: ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ስለ አንቺ ሁሉንም ነገር ስለሚያውቅ፣ ጥሩና ደስተኛ ልጅ ሊያደርግሽ ፈለገ:: ስለዚህ በስምሽ ጠራሽ:: አንቺም እርሱ መሆኑን አወቅሽና ወደ እርሱ በመምጣት ፍጹም ዋስትና እንዳለሽ ተሰማሽ::»

«ለሁለት ቀን ብቻ፣» አለች ጄኒ::

«አዎ፣ ትክክል ነው:: ኪንዛ የገጠማትም እንዲህ ያለ ሁኔታ ነው:: የእንጀራ አባቷ መናገር ከመጀመሩ ሁለት ደቂቃዎች ቀደም ብሎ እቅፌ ውስጥ አልነበረችም:: ድምጼን ስትሰማ መንፈራገጥና ማልቀስ ጀመረች:: በጣም እቅፍ አደረግኳት፣ ወደድኳት:: የሠረቃትንና የደበደባትን ሰውዬ ድምፅ በሰማች ጊዜ ግን ወዲያውኑ መፍራት ጀመረች:: ችግሯ የተወገደላት መሆን አለመሆኑንም በጥርጣሬ ታስብ ጀመር:: አንዳንድ ጊዜ ያወቅነው ወይም የሰማነው ነገር እውነት ስለ መሆኑና ስላለመሆኑ እንጨነቅና እንፈራ ይሆናል:: ነገር ግን፣ ስሜቶቻችን ምንም አይደሉም፤ ምክንያቱም ኢየሱስ አይለወጥም:: ተጨነቅንም አልተጨነቅንም፣ በደንብ ያቅፈናል፣ በጣም ይወድደናል::»

«ገባኝ፣» አለች ጄኒ እያሰላሰለች::

«ከዚያ በኋላ ስለሆነው ነገር ልንገርሽ አዳምጪ:: ወደ ሲ. መሐመድ ቀረብኩና ከኪሴ ገንዘብ አውጥቼ ከፈልኩት:: ኪንዛ ያደገችና የሚገባት ቢሆን ኖሮ፣ እንዲህ እላት ነበር:: «አትፍሪ ኪንዛ፣ ዋጂቼሻለሁ ወይም እንደገና ገዝቼሻለሁ:: ከእንግዲህ ማንም ከእኔ አይወስድሽም:: ለዘላለም ልጄ ነሽ::» በሹክሹክታ የነገርኳት ግን እንዲህ ብዬ ነው:- 'አትፍሪ ኪንዛ፣ አሁን የእኔ ልጅ ነሽ::' እርሷም ብልህነት ያለበት ነገር አደረገች:: አመነችኝ፣ ፍርሀቷን ተ ወች:: ያ ጩካኝ ሰውዬ እየተናገረ አፉቷ ቢቆምም እንኳ፣ ወደ እኔ ጥብቅ ብላ እቅፌ ውስጥ ተኛች፡ በጉዟችን ጊዜ ሁሉ አንቀላፋች::



ፍርሀትን የማስወገጃው ብቸኛ መንገድ፣ ኢየሱስ የሚናገረውን ማመን ነው:: በፋሲካ እሑድ ዕለት ከሞት ተነሣ:: ይህን ያደረገው የጥሪ ድምጹን ሰምተው ወደ እርሱ በሚመጡ ሰዎች ልብ ውስጥ ለመኖር እንዲችል ነው::»

ጄኒ አክስቷ የነገረቻትን ነገር ሁሉ እያሰላሰለች በዝምታ ቁጭ አለች:: የሆነውን ነገር ስለ ተረዳች፣ በጣም ደስ ብሏታል:: ኢየሱስ ወዷታል፣ ሞቶላታል፣ ዕዳዋን ከፍሎላታል፣ ጠርቷታል፣ እንዲሁም የራሱ አድርጓታል:: ማድረግ ያለባት ብቸኛ መንገድ ወደ እርሱ መቅረብና በእርሱ ማመን ነው::

ከዚያ በኋላ ለትንሽ ጊዜ ሲነጋገሩ ቆዩ:: በመሀሉ ኪንዛ ከእንቅልፏ ነቅታ ቁርስ እንዲሰጣት ጠየቀች:: በዚህ ጊዜ ጄኒ እየዘለለች እናትና አባቷን ፍለጋ ሄደች:: ሮዝመሪ ደግሞ በጾጥታ ተቀምጣ የተሰጣትን ወተት ጭልጥ አድርጋ በመጠጣት ላይ የነበረችውን ልጇን ትመለከት ጀመር::

ባለፉት ጥቂት ቀናት ስታሰላስል ቆይታ፣ ኪንዛ ከእንግዲህ ከእርሷ ጋር ብትኖር ነገሩ አስተማማኝ ሊሆን እንደማይችል እርግጠኛ ሆናለች:: እንጀራ አባቷ ገንዘብ በፈለገ ቁጥር እየመጣ ልጄን መልሺልኝ ሊል ይችላል:: ለሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት እርሱ ሊያገኛት ወደማይችልበት ስፍራ መወሰድ አለባት:: ስፍራውም የጄኒ የዐይነ ሥውራን ትምህርት ቤት ነው::

ይህም ሆኖ አክስት ሮዝመሪ ከምንም ይበልጥ የፈለገችው ኪንዛን በትንሽነቷ ኢየሱስን እንድትወደው እሚያስተምራት ሰው ቤት እንድታድግ ነው:: ለዚህ ፍላጎቷ መልስ የሚሆነውን ነገር በግልጽ ታውቃለች:: ኪንዛን እንድታስተምራት ጄኒን መጠየቅ፣ እንዲሁም ጄኒ ማለት የሚገባትን ነገር የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲያስተምራት መጸለይ::

# ምዕራፍ ሃያ

# መለያየቶች እና ዕቅዶች



ኪንዛ አብራቸው የምትሄድ መሆኑ በተነገራት ጊዜ፣ ጄኒ በደስታ ፈነደቀች፣ እንደ ጥጃ እንቦሳ ዘለለች:: በጉዞዋ ላይ ኪንዛን ማን ይንከባከባታል የሚለው አሳብ ብዙም ስላሳሰባት፣ ጄኒን ለመሰናበት አክስት ሮዝመሪን አልከበዳትም:: ስንብቱም ለረጅም ጊዜ አልነበረም:: አክስት ሮዝመሪ በበጋው ሰሞን ለእረፍት ወደ አገሯ ስለምትሄድ እነርሱ ወዳሉበት ሄዳ ከሁሉም ጋር ለመቆየት ቃል ገብታለች::

ጄኒ ጉዞ ከሚጀምሩበት ምሽት ቀደም ብላ ኪንዛንና አክስቷን ለመጨረሻ ሽርሽር ወደ ተራራው ይዛቸው ሄደች:: በመጥለቅ ላይ የነበረችውን ፀሐይ እየተመለከቱ ለትንሽ ጊዜ ቁጭ አሉ::

«ኪንዛ ትሄዳለች አልሽኝ አክስቴ?» አለች ጄኒ ፈጠን ብላ::

«አዎ፣ ትሄዳለች:: በጣም ብትናፍቀኝም፣ ስለ እርስዋ በጣም ደስታ ይሰማኛል:: ኪንዛ ከሁሉም በላይ በትንሽነቷ ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅን እና መውደድን እንድትማር እፈልጋለሁ:: አሁን አንቺ ኢየሱስን አውቀሽዋል፣ ታስተምሪያታለሽ:: ዐይነ ሥውራን



ትምህርት ቤት ውስጥ ገብታ አንድ ነገር ትማራለች ብዬ እጠብቃለሁ:: እንዲህ ያለች ትንሽ ሕፃን ግን አንድ የተለየ አስተማሪ ትፈልጋለች::»

«እኔ እራሴ ይህን ያህል አላውቅም፣» አለች በጥርጣሬ ስሜት፤ «ማን ያስተምረኛል፣ አክስት ሮዝመሪ? ትምህርት ቤታችን ውስጥ እንደ አንቺ አይናገሩም፣»

«አዎ፣ አስቸጋሪ ይመስላል:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስላለሽ፣ በጣም ጥሩ ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ መንፈስ በልብሽ ውስጥ አለ፣ እርሱ የምታነቢውን ነገር ትርጉም እንድትገነዘቢ ይረዳሻል::»

«አንዳንድ ረጃጅም ቃላት አሉበት፣» አለች ጄኒ አሁንም በመጠራጠር ስሜት::

«እናትና አባትሽን ብትጠይቂያቸው ከባድ ቃላትን ሊገልጡልሽ ፈቃደኛ እንደሚሆኑ እርግጠኛ ነኝ:: አንቺ የምትወጂውን ሁሉ ይወድዳሉ:: ምን እንደ ገጠመሽና ለምን መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ እንደምትፈልጊ ነግረሻቸዋል?»

«አልነገርኳቸውም:: ልነግራቸው ፈልጌ ነበር፣ ግን አልቻልኩም፣» አለች ጄኒ፣ ፊቷን ኮስተር አድርጋ::

«በቃል ብትነግሪያቸው ጥሩ ይሆናል:: ከዚህ የሚበልጠው ጠቃሚ መንገድ ግን የተለወጥሽ ልጅ መሆንሽን፣ እንዲሁም ኢየሱስ ቁጡነትሽንና ራስ ወዳድነትሽን የለወጠው መሆኑን በተግባር ማሳየት ነው:: ይህ መሆን ሲጀምር እናትና አባትሽ ማንም ሳይነግራቸው ወዲያውኑ ያውቃሉ::»

«አዎ፣ ጥሩ ልጅ ብሆንና ቁጣዬን ብተው በእርግጥ ደስ ይላቸዋል:: ለምን እንዲያ እንደ ተለወጥኩም ለማወቅ ይፈልጋሉ:: ስለዚህ በመጀመሪያ መለወጤን በተግባር ባሳያቸው ይሻላል:: ከዚያ በኋላ ስነግራቸው ያምኑኛል:: አሁን ወደ ቤት እንሂድና ለጉዞ ዕቃ በማዘጋጀቱ ሥራ ላግዛቸው መፈለጌን ላሳያቸው፣» አለች ጄኒ በመስማማት አነጋገር::

በሚቀጥለው ማለዳ ለመሰነባበት ሁሉም ሆቴሉ በር ላይ ተሰበሰቡ:: ሀሚድም ትንሽ እኅቱን ለመሰናበት መጥቷል:: የጄኒ እናትና አባት ሂሳብ በመክፈልና ከዕቃ ተሸካሚዎች ጋር ወዲያ ወዲህ በማለት ሥራ በዝቶባቸዋል:: አክስት ሮዝመሪ ዝግጅቱ እስኪጠናቀቅ ቆማ በመጠበቅ ላይ እያለች፣ ካወቀቻቸው ልጆች ሁሉ አብልጣ የወደደቻቸውን ሦስት ሕፃናት ትመለከታቸዋለች:: ሻንጣዎቹ አጠገብ ስብስብ ብለው ቆመዋል፣ ቆንጆዋና ሀብታሟ ጄኒ፣ እንዲሁም ቡቱቱ ለባሹ ሀሚድና ዐይነ ሥውሯ ኪንዛ:: የወደፊት ዕጣቸው ምን ይሆን? ብላ አሰበች:: የኢየሱስ የፍቅር ብርሃን ስሚመራቸውና ከክፉ ስለሚጠብቃቸው እግዚአብሔርን አመሰገነች:: አንድ ቀን ሁሉም መንግሥተ ሰማያት ይገናኛሉ::

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ቀሪዎቹና መንገደኞቹ ተሰነባበቱ:: መኪናውም ፊቱን ወደ አረንጓዴው ሸለቆ በመመለስ ጉዞውን ቀጠለ:: የጄኒ ዐይኖች እንባ አቅርረው ነበር:: ኪንዛ ግን በደስታ የመኪናውን መስኮት እንደ ከበሮ ትመታለች:: ሮዝመሪ መኪናው ውስጥ አብራት እንደሌለች ገና አላወቀችም:: በምታውቅበት ጊዜ፣ ያለምንም ጥርጥር አንድ ብስኩት ሲሰጧት ትጽናናለች:: መኪናው በጠመዝማዛ መንገድ ታጠፈና ከሸኚዎቹ እይታ ተሰወረ:: ሮዝመሪ ቢያንስ ከልጆቿ አንዱ አጠገቧ መኖሩን ስትረዳ ተጽናናች:: አንድ የሀሚድ ትልቅ የልጅነት ተልዕኮ ሙሉ በሙሉ ተሳካ:: ትንሽ እኅቱ ከእንግዲህ አትፈልገውም:: ጥሩ ጥሩ ልብሶች፣ ትልልቅ መጫወቻ መኪናዎችና ብስኩቶች ይኖሯታል:: አሁን ባዶ ወደሆነው የገበያ ስፍራ፣ ወደ ረሃብ፣ ጎዳና አዳሪነቱና ቡቱቱ ለባሽነቱ መመለስ አለበት::

«ና እንሂድና ቁርስህን ብላ፣» አለች አጠገቡ የቆመችው ነርስ ሮዝመሪ::

ሀሚድ ይህን ሲሰማ ፊቱ ወዲያው በደስታ በራና ችግሮቹን ሁሉ ረሳቸው:: ከቡና የሚሠራው ጣፋጭና ትኩስ መጠጥ፣ እንዲሁም ዳቦና ቅቤ ወደ አእምሮው በመምጣት ዓለምን ደስ የምትል ስፍራ አስመሰላት:: እጆቹን በደስታ እያሻሸ አብሯት ነው የተጓዘው:: ቀጣሪው ወደ ከተማ ስለ ሄደ፣ ዛሬ ሥራ የለውም::



ስለዚህ ብዙ ጊዜ አለው:: ከአሁኑ ግብዣ በተጨማሪ የሚበላ ነገር የማግኘት ዕድል ይኖር ይሆናል::

ቁርስ ሲያበቃ ዕለታዊ የንባብ ትምህርቱን አከናወነ:: በጣም ፈጣን ተማሪ ስለሆነ፣ ነርሷ በጣም ተገርማበታለች:: ብዙ ዓይነት ሕፃናትን አስተምራለች:: የጎዳና ልጆች የመማር ፍጥነት ግን ያስደንቃል:: ቀልድ አዋቂነታቸውና የማስታወስ ችሎታቸው ለመኖር በሚያደርጉት ትግል ተሞርዷል:: አትኩሮ በመመልከትና በማስታወስ ክህሎት ራሳቸውን አሠልጥነዋል:: ሀሚድ በአንድ ሳምንት ውስጥ ፊደሎችን ተማረ፣ የሚደጋገሙ መልመጃዎችንም በቃሉ አጠና:: በዚህ ችሎታውም በጣም መኩራት ጀምሯል::

«አሁን ሁሉንም ነገር አውቄአለሁ፣» አለ ሦስት ፊደሎች ካሏቸው ጥቂት ቃላት ጋር እየታገለ::

«አላወቅክም፣ ሀሚድ:: ገና መጀመርህ ነው:: በፊደሎች ቃላትን እየሠራህ ደጋግመህ መለማመድ አለብህ:: እስከሚቀጥለው የመከር ጊዜ ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን ለመቻል ከፈለግክ በየቀኑ መምጣት አለብህ::»

በልበ ሙሉነት ራሱን በአዎንታ እየነቀነቀ፣ «በመከር ጊዜማ ወደ መንደሬ ተመልሼ የእግዚአብሔርን ቃል ለእናቴ አነብላታለሁ:: ከዚያ እርሷም ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚወስደውን መንገድ ታውቃለች:: እንጀራ አባቴ ቢደበድባትና በቂ ምግብ ባይሰጣትም፣ ጌታ ኢየሱስ ልቧን ደስ እንዲለው ያደርጋል::»

«የእግዚአብሔርን ቃል እንድታነብላት እንጀራ አባትህ ይፈቅድልሃልን?»

«አይፈቅድልኝም:: ቢሆንም፣ እናቴ በወፍጮ በቆሎ በምትፈጭበት ጊዜ አነብላታለሁ:: ለእኅቴ ለራህማ ደግሞ ተራራዎች ላይ አብረን ፍየሎችን በምንጠብቅበት ጊዜ እንዲሁ አነብላታለሁ:: እንጀራ አባቴ በፍጹም አያውቅም::»

«ሀሚድ ኢየሱስን በታማኝነት የምትከተለው ከሆንክ፣ እርሱም ቆይቶ በኋላ ማወቅ አለበት:: ልትነግረው ይገባል፣ በዚህም

ምክንያት ይመታህ ይሆናል። ቢሆንም፣ ኢየሱስ ስለሚወድህ ለአንተ ሲል በጣም ተሠቃይቷል። ኢየሱስን ከወደድከው፣ ለእርሱ ስትል አንተም በትንሹ ለመሠቃየት ፈቃደኛ መሆን አለብህ።»

ትኩር ብሎ እያያት፣ «በጣም እወድደዋለሁ፣» አለና ሮዝመሪን ካስደሰታት መልሱ ጋር በመተው ለመሄድ ብድግ አለ።

ሀሚድ ንባብ የቻለው ብዙም ሳይቆይ ነበር። በርትቶ አጠና። ሮዝመሪም በዳቦና በምሥር ወጥ የተዘጋጀ የመሰናበቻ ግብዣ ስታዘጋጅለት ብዙ ጊዜ የወሰደባት አይመስልም።

ሀሚድ የሚጓዘው ብቻውን አልነበረም፣ ጥቂት የጉዞ ጓደኞች ነበሩት። ከሌሎቹ ይበልጥ ርቆ የሚጓዘው እርሱ ነው። የሚመራውንና ከክፉ ነገር የሚከለክለውን አዲስና የከበረ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ከደረቅ ዳቦዎች፣ ከውኃ ጠርሙስ፣ እንዲሁም እንጀራዎች ጋር ይዟል። እንዲህ የሚለው የኢየሱስ ተስፋ ነበረው፣ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፣ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም።»

ሮዝመሪ፣ ሀሚድና የጉዞ ጓደኞቹ ፈጣን ጉዟቸውን ሲጀምሩ ትመለከታቸው ነበር። መንገዱ ጫፍ ሲደርሱ ሁሉም ዘወር ብለው እጆቻቸውን አውለበለቡላት፣ ከፊት ለፊታቸው ካለው ሰማይ አንጻር ጥቋቍር ቅርጾች ሆነው የሚታዩ አምስት ትንንሽ ፍጥረቶች። ከዚያም በመንገዱ ማዕዘን እጥፍ አሉና ግርማዊ ብርሃን ባለው የፀሐይ ጥልቀት ውስጥ ተሰወሩ።



## ይህንን መጽሐፍ ላነበቡ ልጆች. . .

ፓትሪሺያ ስንጀን የምወዳት ጓደኛዬ ነበረች። የጻፈቻቸው ታሪኮች እውን በሆኑ ሰዎችና ሁነቶች ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን አውቃለሁ። በመሆኑም፣ በዚህ መጽሐፍ የተገለጹት አብዛኛዎቹ ነገሮች እውነት ናቸው። ፓትሪሺያ ከምታውቃቸውና አብረዋት ከሠሩ ሰዎች ሕይወት ብዙ ሁነቶችን ሰብስባ በዚህ ታሪክ ውስጥ ሸረበቻቸው።

ሰሜን አፍሪካ ውስጥ ለብዙ ዓመታት የሠራች ሚስዮናዊት ነርስ ናት። ታሪኩ ውስጥ እንዳለችው አክስት ሮዝመሪ ተራራ ላይ ባለች ከተማ አንዲት ጐጆ ውስጥ ኖራለች። ቤቷ ለጎዳና ልጆች፣ በተለይ ለወንዶቹ «ክፍት» ነበር። የሕክምና እርዳታ ፍለጋ ወደ ቤቷ የሚመጡ ብዙ ሰዎችን ለመርዳት ሞክራለች። አንዳንዶቹ ከአድካሚ ርቀት የተጓዙ ነበሩ። ለሀሚድ እንዳደረገችው፣ ችግረኞች ሰዎችን ለመርዳት በተራራማው አገር ብዙ ርቀት በእግሯ ተጉዛለች።

ይህ ታሪክ በአንዳንድ መንገድ አሳዛኝ ታሪክ ቢመስልም፣ ፓትሪሽያ የጻፈችው በድሀ አገሮች የሚኖሩና ስለ ኢየሱስ ያልሰሙ ብዙ ልጆችን ሕይወት እውነተኛ ሥዕል ለመግለጥ ባላት ዓላማ ነው። በኀዘን መሀል ተስፋና ደስታ አለ። እንደ ሀሚድ ያሉ ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ወደ ልባቸው በመጋበዝ ለወንጌሉ መልእክት አጸፋ ሰጥተዋል። ሕይወታቸውም ወደ መልካምነት ተለውጧል።


ፓትሪሽያ፣ መልካም ዕጣ ያልገጠማቸውን ሰዎች ሕይወት በመንገር አንባቢዎቿ፣ ለችግረኞቹ ሊጸልዩላቸውና የኢየሱስን ርኅራኄ፣ እንዲሁም ፍቅር ሊያሳዩዋቸው ይበረታታሉ በማለት ተስፋ ታደርጋለች። በብዙ የዓለም ክፍሎች ያሉ ችግረኛ ሕፃናትን የሚረዳና በቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተ ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ የተራድኦ ድርጅት ፕሬዚዳንት ሆና አገልግላለች።

ፓትሪሽያ በነርስነት ያገለገለችበት ድርጅት የአረቡ ዓለም አገልግሎት (Arab World Ministries) በመባል ይታወቅ ነበር። ድርጅቱ አሁንም ለሕፃናትና ለአዋቂዎች የኢየሱስን መልካም የምሥራች በማካፈል ለድነታቸው በመሥራት ላይ ነው።

ሜሪ ሚልስ

## በፓትሪሺያ ስን ጆን የተጻፉ ሌሎች አስደሳች መጻሕፍት:-

## አስደናቂው የይቅርታ ቅርስ





አኔት፣ ሉሲየን በዳኒ ላይ ስላደ ረሰው ጉዳት ይቅርታ ልታደርግለት እንደማትችል ታውቃለች:: ማንም ሰው ይቅርታ እንዳያደርግለት የምትችለውን ያህል ትጥራለች:: ነገር ግን፣ በሁለቱም ሕይወት ውስጥ አንድ አስደናቂ ነገር መሆን ጀመረ ...

ይህንን መጽሐፍ በአቅራቢያዎ ካለ ክርስቲያናዊ መጻሕፍት መደብር መግዛት ይችላሉ፤ ወይም ኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ፣ የፖ. ሣ. ቁ. 127፣ አዲስ አበባ ብለው ይጠይቁን::



## የአራተኛው ሻማ ምሥጢር

ይህ መጽሐፍ ሦስት አጫጭር ታሪኮችን የያዘ ነው:: አብነት ትልቁ ቤት ውስጥ አራተኛው ሻማ በሚበራበት ጊዜ ወደዛ ለመሄድ ብትፈልግም፣ አልቻ ለችም:: እትዬ በለጡ በትንሹ እንግዳ መምጣት ተደንቀዋል:: መልካሙ ኩታውን ለታመመችው ልጅ በማበደሩ ደስታ ተሰምቶታል::




ይህንን መጽሐፍ በአቅራቢያዎ ካለ ክርስቲያናዊ መጻሕፍት መደብር መግዛት ይችላሉ፤ ወይም ኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ፣ የፖ. ሣ. ቁ. 127፣ አዲስ አበባ ብለው ይጠይቁን::